ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 057 ጥቅምት 27 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር
በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

# “የሠላሙ ሁኔታ ይበልጥ ሲስተካከል አንዱ ተግባራችን ወደ ትግራይ ክልል መሄድ ነው”

- ፕሮፌሰር መስፍን ዓርአያ
የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሰብሳቢ



ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የሠላሙ ሁኔታ ይበልጥ እየተስተካከለ ሲመጣ አንዱ ተግባራችን የሚሆነው ወደ ትግራይ ክልል ሄደን ሕዝቡን እስከታች ድረስ ማወያየት ነው ሲሉ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሰብሳቢ ፕሮፌሰር መስፍን ዓርአያ አስታወቁ።

ፕሮፌሰር መስፍን ዓርአያ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መላው ኢትዮጵያውያን የተሳካ የምክክር ሂደት እንዲያከናውኑ የትግራይ ሕዝብ ተሳታፊነት አስፈላጊ ነው።

የፌዴራል መንግስትና ሕወሓት ያደረጉት የሠላም ውይይት እኛም ቀድመን ስንፈልገው የነበረው ጉዳይ ነው ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፤ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም አገራዊ ምክክሩን በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

በትግራይ ክልል ያለው ሠላም እየተሻሻለ ሲሄድ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑም በክልሉ ከሚገኘው ሕዝብ ጋር አስፈላጊውን ውይይት ለማድረግ ፍላጎት እንዳለው ገልጸዋል።

እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ከሆነ፤ የምክክር ኮሚሽኑ ቀጣይ ስራዎች የተሳለጠ ለማድረግ በተለያዩ ክልሎች ከሚገኙ የአስተዳደር አካላትና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ውይይት እየተደረገ ነው።

“የሠላሙ ሁኔታ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ
Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት

# በኢትዮጵያ የ‹‹ምናባዊ ገንዘብ›› ግብይት የተጋላጭነት ጥናት እየተካሄደ ነው



አቶ ብሌን ጊዜወርቅ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

አዲስ አበባ፡- ቢትኮይን፤ ክሪፕቶ ከረንሲ እና የተለያዩ ስያሜ የተሰጣቸው ምናባዊ የገንዘብ ግብይቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በምን ደረጃ እየተስተዋለ እንደሆነና የተጋላጭነት ደረጃን የሚያመላክት ጥናት በዓለም ባንክ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪነት እየተጠና መሆኑ ተገለፀ፡፡ የውጭ ሀገር የፋይናንስ ተቋማት ወደ ኢትዮጵያ ገብተው የሚንቀሳቀሱበት ዕድል ከተፈጠረም የፋይናንስ ወንጀሎች ለመከላከል የህግ ማዕቀፍ ለማዘጋጀት እየተሰራ መሆኑም ተጠቁሟል፡፡

የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ብሌን ጊዜወርቅ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በርካታ ሀገራት በተለይም ያደጉ ሀገራት በእኛ ሀገር ቢትኮይን፤ ክሪፕቶ ከረንሲ እና የተለያዩ ስያሜ የተሰጧቸውንና በሙያዊ አጠራር ደግሞ ቨርቹዋል ወይንም ምናባዊ ገንዘብ በተመለከተ ሀገራት በየራሳቸው ህግና ቁጥጥር አበጅተው በህጋዊ ፈቃድ እየሰሩ ነው፡፡ በየሀገራቱም ከፋይናንስ ሥርዓታቸው ጋር አጣጥመው እየሰሩበት ሲሆን፤ በርካታ የአፍሪካ ሀገራትም ይህን

በኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ዶክተር ዮናስ አሸኔ

## የኢትዮጵያ የውስጥ ችግር መፈታት በቀጣናውና በአህጉር ደረጃ የሚጠቀባትን የመሪነት ሚና እንድትወጣ ያስችላታል

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በኢትጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሠላም ስምምነት ኢትዮጵያ የውስጥ ችግሯን ቀርፋ በቀጣናው ብሎም በአህጉር ደረጃ የሚጠበቅባትን የመሪነት ሚና እንድትወጣ

የኢትዮጵያ የውስጥ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በመዲናዋ በያዝነው ወር መጨረሻ የመማሪያ መጽሐፍት ሕትመት ሙሉ በሙሉ ይጠናቀቃል

- እስካሁን ከ1 ነጥብ 2 ሚሊዮን በላይ መጽሐፍት ተሰራጭተዋል

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በያዝነው ወር መጨረሻ ድረስ የመማሪያ መጽሐፍትን ሕትመት ሙሉ በሙሉ አጠናቆ ለማሰራጨት እየሠራ መሆኑን አስታወቀ፡፡ እስካሁን ድረስ አንድ ነጥብ

በመዲናዋ በያዝነው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ ታይልስ ኤጋ መደበኛ ኮልሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

የወዳጅነት ምዕራፍ ሁለት ፓርክ ማንኛውም ልማት የሕዝብ እንደሆነ ያረጋገጠ ነው
- ፓርኩን በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች እየጎበኙት ነው
ገጽ 2

# አዲስ የህይወት ምዕራፍ በአዲሱ የወዳጅነት ፓርክ

ጌትነት ምህረቴ



በአሸበረቀውና በተዋበው በአዲሱ ወዳጅነት ምዕራፍ ሁለት ፓርክ ውስጥ ጥንድ ጥንድ ሙሽሮች በሚዜዎቻቸው ታጅበው እዚህም እዚያ ፎቶ ይነሳሉ። በስፋራው ውበትና ማራኪነት የተገረሙና የተደነቁ ሙሽሮች በየቦታው ፎቶ ሲነሱ ተመለከትኩ። ሙሽራ አብርሃም ለገሰና ባለቤቱ ሙሽሪት መሰረት ፋና ከነዚህ መካከል ናቸው።

እነዚህ ጥንዶች ፊታቸው እንደ ብርሃን ፈክቷል፤ወጣት አብርሃም ህልሙን አሳክቶ ከጎኑ የትዳር አጋሩን ሙሽሪት መሰረትን አቁሟል። አቶ አብርሃምና ወይዘሪት መሰረት እዚህ ስፍራ የተገኙት ሊሞሽሩ ነው። አዲስ ትዳር መስራቾች ናቸው። ዕለቱ በእነርሱ የማይረሳ ነው። ወደ አዲስ ምዕራፍ የገቡበት ከሁለት ወደ አንድነት የተሸጋገሩበት፤አብሮ ለመኖር የተሰረጉበት ዕለትና ስፍራ በመሆኑ ልዩ ክብር ይሰጡታል።

"ቀበሌ ሄደን የጋብቻ ሰርተፊኬት ለማግኘት ተመዝግበን ነበር፤ ድንገት በአዲሱ የወዳጅነት ፓርክ ልትሞሽሩ ተመርጣችኋል ብለው በስልክ ሲነግሩን አላማንኩም። እኔ ወጪውን በመፍራት ሰርግ ለማድረግ አላሰብኩም ነበር። እወቁልኝ በሚል ላልፈው ወስኜ ነበር" የሚለው ሙሽራ አብርሃም፤በአዲሱ የወዳጅነት ፓርክ የሰርግ ስነ ስርዓቱ መካሄዱ ከምገልጸው በላይ በጣም ደስ ብሎኛል፤ ከጠበኩት በላይ በጣም የሚገርም የሰርግ ስነ ስርዓት ነው ብሏል።

አቶ አብርሃም "የምወዳትን ሴት አምላክ ሰጥቶኛል፤ በሰርግ ስነ ስርዓቱም ደስተኛ ነኝ፤ትዳር አዲስ የህይወት ምዕራፍ ነው። በአማረ ቦታ ተሞሽሬአለሁ፤ የትዳር ህይወቴም ጥሩ እንደሚሆን እምኖለው፤እንደ እኔ ሁሉ እዚህ ውብና አረንጓዴ ስፍራ በአንድ ላይ የተሞሸርን ሙሽሮችም የስኬት ዘመንና መልካም ጋብቻ እንዲሆንላቸው ተመኝቻለሁ" ሲል መልዕክቱን አስተላልፏል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በተገኙበት በአዲሱ ምዕራፍ ሁለት የወዳጅነት ፓርክ ከተሞሸሩት ኢትዮጵያውያን መካከል የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ባልደረባ የሆነው ጋዜጠኛ የሱፍ እድሪስ አንዱ ነው።

ጋዜጠኛ የሱፍ እድሪስ የሰርጉን ስነ ስርዓት በተዋበና በአሸበረቀ መልኩ አካሂዳለው የሚል ሀሳብ እንዳልነበረው ገልጾ፤ዕድሉን አግኝቶ የሰርጉን ቀን በአዲሱ የወዳጅነት ፓርክ ሁለተኛ ምዕራፍ ማካሄዱ ደስተኛና ታሪካዊ መሆኑን ተናግሯል።

እንኳን ለዚህ አስደሳችና በህይወታችሁ ትልቅ ምዕራፍ ቀን አበቃችሁ፤ እንኳን ደስ አላችሁ፤ መልካም ጋብቻ እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ ያሉት የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ፤ለሙሽሮቹም ሰርጋቸው የተካሄደበት ስፍራ ለከተማችን ተጨማሪ ውበት፤ ቤተሰብ የሚመሰረትበትና ከጋብቻ በኋላ የሚወለዱ ህጻናት ትምህርት የሚማሩበት፣ክህሎት የሚቀስሙበትና የሚጫወቱበት ነው ብለዋል።

በአዲሱ ምዕራፍ ሁለት የወዳጅነት ፓርክ ሙሽሮች በአንድ ላይ ሲሞሸሩም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ታድመዋል።

"ጋብቻ የሀገር መሠረት ከሆኑት ተቋማት አንዱ የሆነው ቤተሰብ የሚመሠረትበት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የወዳጅነት ፓርክ ምዕራፍ ሁለትን በከፈትንበት ዕለት በሥርግ ዐጸዱ ጋብቻችሁን የፈጸማችሁ ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ። ኢትዮጵያውያን በሀገራችን፣ ሌሎችም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ዓለም አቀፍ፣ ሀገራዊና ማኅበራዊ ክንውኖች የሚፈጸሙበትን ድንቅ ስፍራ በሠርጋችሁ ደስታ አድምቃችሁ አስጀምራችኋል ሲሉ ገልጸዋል።

ሙሽሮቹ በሚያምረው መናፈሻ መሞሸራቸው እንዳስደሰታቸውና ሰርጋቸውን ልዩ እንዳደረገው ተናግረዋል። ሙሽሮቹ በህይወታችን ልዩ በሆነችው ቀን ይህንን ታሪካዊ ሰርግ ላዘጋጀው አካል ምስጋና እናቀርባለን ብለዋል።

በአሸበረቀውና በተዋበው ፓርክ ሙሽሮቹ ሰርጋቸውን ማካሄዳቸው ደስታቸው ወደር እንደሌለውና ከከፍተኛ የሰርግ ወጪም እንደታደጋቸው ገልጸዋል። ሙሽሮቹ ጋብቻቸውን ፈጽመዋል። ኬክ ቆርሰዋል።



ወይዘሮ እታፈራሁ መላኩ



አቶ ሲሳይ እጀታ



ብርሃኑ ካሳዬ



ወይዘሮ ሙና ብርሃኑ

ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

# የወዳጅነት ምዕራፍ ሁለት ፓርክ ማንኛውም ልማት የሕዝብ እንደሆነ ያረጋገጠ ነው

## - ፓርኩን በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች እየጎበኙት ነው

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- የወዳጅነት ምዕራፍ ሁለት ፓርክ ማንኛውም ልማት የሕዝብ እንደሆነ ያረጋገጠ መሆኑን ጎብኚዎች ተናገሩ። ፓርኩን በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች እየጎበኙት ነው።

የወዳጅነት ፓርክን ከጎበኙት መካከል ወይዘሮ እታፈራሁ መላኩ እንዳሉት፤ በአገራችን ሰላም ተፈጥሮ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ልጆች ሲዝናኑ ማየት ትልቅ እድል ነው። የልጆች ቀጣይ ህይወት የደስታና የፍስሃ ዘመን ማሳያ ነው። ሀብታም ደሃ ሳይባል ሁሉም እኩል በነጻነት መጎብኘትና መዝናናት በመቻሉ እንደ ሀገር መልካም ጅምር ነው ያሉት ወይዘሮ እታፈራሁ፤ይህም በቀጣይ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ይህ እውን እንዲሆን ላደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ምስጋናቸውን ገልጸዋል።

ሌላኛው ወላጅ አቶ ብርሃኑ ካሳዬ እንደሚሉት ደግሞ እስካሁን በሀገራችን ይህ አይነት የመዝናኛ ቦታ ባለመኖሩ ተጎድተናል፤ ከለውጡ ወዲህ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ሀሣብ አፍላቂነት የተገነቡት ፓርኮች በሀገራችን ያልተለመደ አዲስ የታሪክ ክስተት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

‹‹በህይወት ዘመኔ ሁሉም የሚዝናናበት ፓርክ በማየቴ ደስተኛ ነኝ››። ህጻናትም ተደስተዋል፤ ይህም አይተን የማናውቀው ስለሆነ ህጻናት አእምሯቸው ብሩህ እንዲሆን የሚያደርግ ነው ብለዋል።

ፓርኩ ለማመን የሚከብድ አስደማሚ የሆነ ፕሮጀክት ነው የሚሉት ደግሞ በፓርኩ ጉብኝት ሲያደርጉ ያገኘናቸው ወይዘሮ ሙና ብርሃኑ ናቸው። ወላጆች ልጆቻቸው ሲደሰቱ ከማየት የበለጠ ምንም ነገር የለም። በቀጣይም መሰል ፕሮጀክቶች በሌሎች አካባቢዎች ቢገነቡ መልካም መሆኑን ተናግረዋል።

ከለውጡ ወዲህ እየተከናወኑ ያሉ ፕሮጀክቶች የሚያስደንቁ ናቸው ያሉት ደግሞ ሌላኛው አስተያየታቸውን የሰጡት አቶ ሲሳይ እጀታ፤ ሁሉንም የህብተሰብ ክፍል ያካተተ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ የወዳጅነት ፓርክ ምዕራፍ ሁለት ምስክር እንደሆነ ገልጸዋል። ማንኛውም ልማት የሕዝብ እንደሆነ ያረጋገጠ ስለመሆኑም አንስተዋል። ይህንም በትክክል አይተናል። ፓርኩ ህጻናትን፣ ወጣቱንና አዋቂውን ያካተተ ነው። ይህ ሲሆን ወጣቱ በአልባሌ ቦታ እንዳይውል ያደርገዋል ይላሉ።

ሳይንስ ሙዚየምን ጨምሮ ሌሎች ሜጋ ፕሮጀክቶችን እንደጎበኙ የገለጹት አቶ ሲሳይ፤ ይህ አይነት የመዝናኛ ስፍራ በሀገራችን ያልተለመደ አዲስ የለውጥ ምዕራፍ ነው። ተግባሩ በልዩ ትኩረት እስከ ክልሎች ድረስ መሠራት እንዳለበትም ተናግረዋል። ፕሮጀክቶቹ ልጆች በሀገራቸው ተስፋ እንዲሰንቁ ለማድረግ ወሳኝ ነው ያሉት ጎብኚው፤ የሀገር ግንባታ የሚጀምረው ዛሬ ለልጆቻችን በምንሰራው ሥራ ነው። እያንዳንዱ ወላጅ ለልጆቹ ትኩረት በመስጠት በመልካም ስነምግባር ታንጸው እንዲያድጉ እንደ ወዳጅነት ፓርክ ያሉ ቦታዎችን ማስጎብኘት አለባቸው ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማን ገፅታ ከቀየሩ ፕሮጀቶች አንዱ የወዳጅነት ፓርክ ሲሆን የዚሁ ፕሮጀክት አካል የሆነው ምእራፍ ሁለት ግንባታው ተጠናቆ ባለፈው ሳምንት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተከፍቶ ለጎብኚዎች ክፍት የሆነ ሲሆን በእለቱ 50 ጥንዶች በሰርግ አጸዱ መሞሽራቸው የሚታወስ ነው።

የምዕራፍ ሁለት የወዳጅነት ፓርክ በ11 ሺ ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን በውስጡ የህጻናት መጫወቻ ስፍራ፣ የወጣቶች የስፖርት ስፍራ፣ የሰርግ አጸድና ሌሎች መዝናኛዎችን የያዘ ለጎብኚዎች ምቹ የሆነ ቦታ ነው።

# ፍርድ ቤቱ የላቀ ሥራ አፈጻጸም ላስመዘገቡ ዳኞችና ባለሙያዎች እውቅና ሰጠ

## -ከ128ሺህ በላይ መዛግብት እልባት ተሰጥቷል

ዋቅሹም ፍቃዱ



አቶ ፉዓድ ኪያር

አዲስ አበባ፡- የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በ 2014 ዓ.ም የላቀ ሥራ አፈጻጸም ላስመዘገቡ ዳኞችና ባለሙያዎች እውቅና ሰጥቷል። ፍርድ ቤቱ በ2014 ዓ.ም ከቀረቡት 145 ሺህ 305 መዛግብት ለ128ሺህ 144 እልባት መስጠቱ ተገልጿል።

ካሉት 12 ምድብ ችሎቶች ተግተው በመሥራት የተሻለ የሥራ አፈጻጸም ላስመዘገቡትና በስነምግባራቸው አርአያ ለሆኑት ለ11 ዳኞች፣ለ11 ረዳት ዳኞች፣ለ11 ሬጅስትራሮች እና ለዳይሬክተሮች እውቅና ተሰጥቷቸዋል።

የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ፉዓድ ኪያር ፍርድ ቤቱ የጀመራቸውን የሪፎርም ሥራዎችን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር ትናንት ምክክር ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ፍርድ ቤቱ አገልግሎት ለማዘመን በተለይ ቀልጣፋ የፍትሕ አሰጣጥ እና የዳኝነት አገልግሎት ለመስጠት ውጤታማ የሆኑ በርካታ የሪፎርም ሥራዎችን አከናውኗል። አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግና ምቹ የሥራ አካባቢን ለመፍጠር በምድብ ችሎቶች የአንድ መስኮት አገልግሎት ጀምሯል፡፡

የቂርቆስና የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተሞች ምድብ ችሎቶች እንደገና እንደ አዲስ ማደራጀታቸውን የገለጹት አቶ ፉዓድ፤ በዚህም በቂርቆስ ምድብ ችሎት የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጥበት ህንጻ ግንባታ ተጠናቆ ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ምድብ ችሎትም ቀድሞ በኪራይ ከነበረበት ቦታ በፍትሕ ሚኒስቴር ለጋራ ዓላማ ወደ ተገነባው ሕንጻ በማዞር የዳኝነት ሥራውን እያከናወነ ይገኛል ብለዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በዓመት እስከ አንድ ሚሊዮን ለሚደርሱ ተገልጋዮች አገልግሎት እንደሚሰጥና ለፍርድ ቤቱ በዓመት እስከ 200ሺህ የዳኝነት ጉዳዮች እንደሚቀርብለት የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ አቅም በፈቀደ መጠን ቀልጣፋ አገልግሎት በገለልተኝነት እንዲሰጥ የማሻሻያ ሥራዎች መዘርጋታቸውን አመልክተዋል፡፡

የዳኞች ገልተኝነት ማለት ዳኞች እንደፈለጉ ወሳኔ የሚሰጡበት አውድ ሳይሆን ገለልተኝነቱ በይበልጥ ሕዝቡ የፍትሕ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑን ያብራሩት ፕሬዚዳንቱ፤ ከዚህ አንጻር በዳኝነት ሥርዓቱ ተጠያቂነት ለማስፈን የዳኞች ስነምግባር መመሪያ ወጥቶ ሥራ ላይ መዋሉን አስታውቀዋል፡፡

በመመሪያው መሰረት የስነ ምግባር ጉድለት የታየባቸው ዳኞችና ረዳት ዳኞችን ከወርሃዊ ደመወዝ ቅጣት ጨምሮ ሌሎች ህጋዊ እርምጃዎችን መወሰዱንም ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የፍርድ ቤቱ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ተስፋዬ ንዋይ እንደገለጹት፤ በውስን የሰው ሀይል ለበርካታ መዛግብት እልባት መስጠት መቻሉ የሪፎርሙ ውጤት ነው፡፡ ያም ሆኖ አሁንም በርካታ ሥራዎች ይቀራሉ፡፡ ለአብነት ያህል በተለያዩ ምክንያቶች ተንከባልለው ስድስት ዓመት ያስቆጠሩ 263 መዛግብት አሉ፡፡ ለእነዚህ መዛግብት በ2015 ዓ.ም የበጀት ዓመት እልባት ለመስጠት ቅድሚያ እንደሚሰጥ አመልክተዋል፡፡

በፍርድ ቤቶች የሰራተኞች ፍልሰት ትልቅ ተግዳሮት መሆኑን የጠቆሙት አቶ ተስፋዬ፤ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ብቻ 300 ሰራተኞች ሥራ መልቀቃቸውንም አንስተዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለስምምነቱ ስኬት ከልብ የመነጨ የሠላም ቁርጠኝነትያስፈልጋል!

በኢትዮጵያ መንግስትና በሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ የተደረገው የሠላም ስምምነት በሀገሪቱ የተጀመረውን ልማት በማስቀጠል የበለጸገች ሀገር ለመፍጠር የሚደረገውን ሃገራዊ ርብርብ እውን በማድረግ ሂደት ውስጥ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ እንደሆነ ይታመናል።

ልማት የአንድን ሃገር እጣ ፈንታ ከመወሰን ባለፈ ፣ የሃገር ክብር መገለጫ በሆነበት ሁኔታ፤ በብዙ ተጋድሎ ያገኘነውን ነጻነት ሙሉ ለማድረግ ልማት ላይ አጠንክረን መስራት ወሳኝ ነው። ለዚህ ደግሞ የሠላማችን ጉዳይ አልፋና ኦሜጋ ስለመሆኑ ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

ላለፉት አራት ዓመታት ድህነትን አሸንፈን በመውጣት የራሳችንን እጣ ፈንታ በራሳችን ለመወሰን በሚያስችል አዲስ የለውጥ ምዕራፍ ውስጥ እንገኛለን። በተለይም በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታትም ለዚህ የሚሆን ሀገራዊ መነቃቃትና ምቹ ሁኔታ መፍጠር ችለን ነበር።

ይሁንና ጥቃትን ለመከላከል ሲባል ወደ ጦርነት ተገድደን ገብተናል። ጦርነቱ እንደሀገር የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለንም የአደባባይ ሚስጥራችን ነው። በአንድ በኩል የገባንበት ጦርነት ሳንፈልገው ተገደን /የሀገርን ህልውና ለመጠበቅ/ የገባንበት መሆኑ፤ በሌላ በኩል ከጦርነቱ በስተጀርባ ብዙ ተዋንያን በአንድም ይሁን በሌላ ተሳታፊ መሆናቸው ጦርነቱ በሁለንተናዊ መልኩ ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል እንዲሆን አድርጎታል።

ጦርነት ከፍ ያለ ሀብት በሚፈልግበት ፣ በራሱ ከሚፈጥረው ውድመት ውጪ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያስከትለው ውድመት የሚፈጥረው ማህበራዊ ምስቅልቅል በራሱ አስከፊ በሆነበት በዚህ ዘመን ጦርነቱ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ የመሆኑ እውነታ ለማንም የሚነገር አይደለም።

ሕዝቢቿን በበቂ ሁኔታ ለመመገብ በየአደባባዮቿ ቃል ለምትገባ፤ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ከከፍተኛ ተቋማት ተመርቀው የስራ ያለህ በሚሉባት፤ የተፈጥሮ ሀብቶቿን አልምታ ስር የሰደደን ድህነት አሸንፎ ለመወጣት የሀብት ያለህ ለምትለዋ የእኛዋ ኢትዮጵያ ጦርነት ሊያስከትል የሚችለው ጥፋት የቱን ያህል የከፋ ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም።

ይህንን ነባራዊ እውነታ ማስተዋል ሳይቻል በእብሪት፣ በእልህና በስሜት መንገድ መጓዙ ሊያስከትል የሚችለው ጥፋት የቱን ያህል ልብ ሰባሪና አውዳሚ እንደሚሆን የታወቀ ነው። የታሪካችንን ሰፊ ስፍራ የያዙት የጦርነት ትርክቶቻችን ናቸው። በቀደሙት ዘመናት ብቻ ሳይሆን ትናንትም እስከ ዛሬ ጠባሳው ያልሻረ ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል። ሃገርን እንደ ሃገር የጉስቁልና ማሳያ በማድረግ ብሄራዊ ክብራችን ላይ ያሳረፈው አሉታዊ ተጽዕኖም ቀላል አልነበረም።

ሕዝባችን በለውጡ ማግስት ለልማት የነበረውን መነቃቃት በማቀዛቀዝ፤ ጦርነቱ የፈጠረው መደነቃቀፍ አሁን ካስመዘገብነው ልማት የበለጠ ውጤት እንዳናመጣ አድርጎናል፤ የኢኮኖሚ ምስቅልቅል በመፍጠርም የሀገርን ውድቀት ለማፋጠን ለሚሹ ኃይሎች መልካም አጋጣሚ ሊፈጥርም ይችል ነበር።

ችግሩ በለውጡ ተስፈኛ በነበረው የትግራይ ሕዝብም ላይ ይዞበት የመጣው መዘዝ በቀላል ቋንቋ ሊገለፅ የሚችል አይደለም፤በብዙ ዋጋ የተገነቡ መሰረተ ልማቶችን በማውደም ለቀጣይ ልማት የሚሆነውን ሀብት በልቶበታል። ነገን ተስፋ ከማድረግ ይልቅ ተስፋ አጥቶ የምሬት ህይወት እንዲገፋ አስገድዶታል።

የሠላም ስምምነቱ በሀገር ልማት ላይ በጦርነቱ ምክንያት አንዣቦ የነበረውን ጽልመት በመግፈፍ የተጀመሩ የልማት ስራዎች በተሻለ ፍጥነት እና አቅም የሚጓዙበትን እድል የሚፈጥር ነው። ሃገርን ቀጣይነት ባለው ልማት ለማበልጸግ የተቀመጠው ራዕይ እውን እንዲሆንም ፋይዳው እጅግ የላቀ ነው።

ጦርነቱ የሃገርን ሀብትና ጥሪት ከመብላት ባለፈ የፈየደው አንዳች ነገር አለመኖሩን በተጨባጭ ከትናንት ተሞክሮው በመማር ራስን ለቀጣይ ሀገራዊ ልማት ማዘጋጀትና ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነት መፍጠር ከሁሉም ይጠበቃል።

ጦርነቱ በፈጠረው ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት ልክ ገምግሞ ለስምምነቱ ስኬት ራስን መግራት እና ተገዥ ማድረግም ጊዜው የሚጠይቀው ወሳኝ ጥያቄ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# በወንድማማች መካከል አሸናፊም ተሸናፊም የለም

ራስወርቅ ሙሉጌታ

በሰሜኑ ክፍል የነበረው ደም አፋሳሽ ግጭት በመጨረሻ በሠላማዊ መንገድ በድርድር እልባት አግኝቷል። የኢትዮጵያ መንግስት የአገሪቱን ሉአላዊነትና ብሄራዊ ጥቅም አስጠብቆ ጉዳዩን ለመቋጨት ችሏል። ከዳር ሆነው የኢትዮጵያን እንደ አንባሻ መቆራረስ በጉጉት ሲጠብቁ የነበሩ ሃይሎች ህልማቸው ከሽፏል። በጦርነት ቀጣና ውስጥ የነበሩት ዜጎች በመጨረሻም እፎይታ ያገኛሉ። እርዳታ የሚሹት የሰብአዊ ድጋፍ ያለምንም እንከን እንዲደርሳቸው የተደረሰው ስምምነት የሚያግዝ ነው።

በሂደት ሁኔታዎች ሲረግቡና ስምምነቱ ተፈፃሚ ሲሆን ደግሞ ሁሉም ዜጎች በሠላም ከመንቀሳቀስ አልፈው ስነልቦናዊ እረፍትን ያገኛሉ ዘመድ ከዘመዱ ይጠያየቃል፣ የመንግስት ሰራተኛው ወደ ቢሮው፣ ገበሬው ወደማሳው፣ ተማሪውም ወደ ትምህርት ቤቱ ይገባል። በዚህ ውስጥ ማንም አሸናፊ ማንም ደግሞ ተሸናፊ አይኖርም።

በዚህ ውስጥ ኢትዮጵያ ታሸንፋለች። የህሊና እረፍት አጥተው በጦርነት እገታ ውስጥ የቆዩ ህፃናት፣ ሴቶችና አዛውንቶች አሸናፊ ይሆናሉ። የሚሰሩ እጆች ነፃ ይወጣሉ። በተደረሰው የሠላም ስምምነት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ያሸንፋል። ያለማንም ጣልቃ ገብነት አፍሪካ ውስጥ የሚከሰቱ ጦርነቶች በንግግርና በድርድር እንደሚቋጩ ትልቅ ማሳያ ይሆናል። በዚህ ሂደት ውስጥ አንድ ወገን ብቻ ሳይሆን አፍሪካ ታሸንፋለች።

ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይህን እውነት በልቦና ውስጥ ሊያስቀምጠው ይገባል። የተደረሰውን የሠላም ስምምነት አስመልክቶ በማህበራዊ ድረገፆች የተለያዩ የሃሰት መረጃዎች እየተነዙ ነው። ምክንያቱ ደግሞ አንድና አንድ ብቻ ነው። የአገሪቱ መረጋጋትና ፊቷን ወደ ልማት ማሸጋገር የማይዋጥላቸው ቡድኖች ስምምነት ባደረጉት አካላትና በህዝቦች ውስጥ ልዩነት የሚፈጥሩ መልእክቶችን እያሰራጩ ነው። በሰላም ስምምነቱ አሸናፊና ተሸናፊ አካላትን ለመፍጠር እየታገሉ ይገኛሉ። ይህንን ማክሸፍ ያስፈልጋል።

በጦርነቱ ወቅት ህዝቦች ጦር አልሰበቁም። እርስ በእርስም የፈጠሩት ግጭት የለም። ይልቁኑ ወደሚያምኑት አምላክ በመፀለይ ሠላም እንዲወርድና መረጋጋት እንዲሰፍን ሰርተዋል። ህዝብ ባልተጋጨበት ሁኔታ "የሠላም ድርድሩ በዚህኛው አካል አሸናፊነት ተደመደመ" የሚል መልእክት ማሰራጨት እና ለዳግም ግጭት ግፊት መስራት አዋጪ አይደለም።

> **አንዳንዶች ደግሞ ፍጹም በሆነ ድንዳኔ የሠላም ስምምነቱን አደባባይ ወጥተው በመቃወም፣ሀገርና ህዝብ ከጦርነት የሚያተርፈው አንዳች ነገር ያለ ይመስል እየጮሁ ይገኛሉ። ከጦርነቱ አካባቢ ርቀው ሁሉ ነገር ሰላም በሆነበት ምድር እያሰሙት ያለው ድምፅ በሀገርና በህዝብ ላይ በአደባባይ ሞት የማወጅ ሟርት እንደሆነ ለማስተዋል ስክነት አላገኙም**

ዜጎችም ለዚህን መሰል ፕሮፓጋንዳ ጆሮ ሊሰጥ አይገባም። በጥቅሉ ልዩነቶችን በጠረጴዛ ዙሪያ ለመፍታት የተደረሰው ስምምነት ሁሉንም አካላት አሸናፊ የሚያደርግ እንደሆነ ሊታመንበት ይገባል። በእውነትም በአግባቡ ከተጠቀምንበት ሁላችንም አሸናፊ የምንሆንበት ነው።

በአፍሪካ ህብረት አደራዳሪነት እንዲሁም በተለያዩ ዓለም አቀፍ አካላት ትብብር የተደረሰውን ስምምነት አስመልክቶ እጅግ በርካታ አወዛጋቢ መረጃዎች የኢትዮጵያን ሠላም በማይፈልጉ አካላት እየተሰራጩ ይገኛል።

ከዚህ ውስጥ አንዱ የተዛባና ከእውነት የራቀ የስምምነት አንቀፆችን የያዘ ሰነድ ይገኝበታል። ይህን መሰል መረጃ ምንጩ ከማይታወቅ አካል በመውሰድና በማሰራጨት ዜጎችን ማወናበድ የቱንም አይነት ሴራ ሊያሳካ አይችልም። ለጊዜው ግርታን የሚፈጥር ቢሆንም ቀስ እያለ የሚጠራ ይሆናል።

አሁን የኢትዮጵያ መንግስት በስምምነት ሰነዱ መሰረት ቀጣይ መርሃ ግብሮችን ተከትሎ የሚተገበረውን እርምጃ ይፋ እስኪያደርግ ድረስ ሁሉም ዜጎች ግርታ ውስጥ ሳይገቡ መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

ይህ ሲሆን ከአላስፈላጊ መወናበድ ያድናል። ምንጩ የማይታወቅ መረጃን ማጥራትም እንዲሁ የዜጎች ኃላፊነት ነው። በማህበራዊ ሚዲያዎች የሚፅፉ አንዳንድ አካላት ውሉን የሳተ ትንታኔ ውስጥ ገብተው ህልማቸውን ለማሳካት ከላይ እታች እያሉ ይገኛሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ለእነዚህ አካላት ጆሮ መስጠት አይኖርበትም።

አንዳንዶች ደግሞ ፍጹም በሆነ ድንዳኔ የሠላም ስምምነቱን አደባባይ ወጥተው በመቃወም፣ሀገርና ህዝብ ከጦርነት የሚያተርፈው አንዳች ነገር ያለ ይመስል እየጮሁ ይገኛሉ። ከጦርነቱ አካባቢ ርቀው ሁሉ ነገር ሠላም በሆነበት ምድር እያሰሙት ያለው ድምፅ በሀገርና በህዝብ ላይ በአደባባይ ሞት የማወጅ ሟርት እንደሆነ ለማስተዋል ስክነት አላገኙም።

በአክቲቪስት ስም የሚያካሂዷቸው አደናጋሪ ዘመቻዎች በቀደመው ዘመን ብዙ ዋጋ እንዳስከፈሉን ሁሉ አሁንም ተጨማሪ ዋጋ እንዳያስከፍሉን መጠንቀቅም ተገቢ ነው። ከዚህም በላይ ዛሬ ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ለደረሰው ችግር እንደ ማህበረሰብ የጀመርነው የብሽሽቅ ፖለቲካ አንዱ መሆኑን ልንዘነጋው አይገባም።

ሃያ ሰባት አመት ይዘነው የመጣነው የብሽሽቅ ፖለቲካና አላስፈላጊ የሆነ ፉክክር በማህበራዊ ሚድያው እየታገዘ የብዙ ችግር ምንጭ ሆኗል። እነዚሁ ሰዎች ዛሬ ለሠላም ስምምነቱ አቃቂር በማውጣት ሕዝቡን ለማሳሳት ረጅም መንገድ እየሄዱ ነው።

ስምምነቱ ሀገርን ከገባችበት አጣብቂኝ በማውጣት ሀገርን እንደ ሀገር መላው ህዝባችንን እንደ ህዝብ አሸናፊ ያደረገ ፣ በዚህም ዘላቂ ሠላም በማምጣት የጀመርነውን ልማት ከፍ ወዳለ ደረጃ አሳድገን ሀገርን በብልጽግና አዲስ የታሪክ ምእራፍ ለመግለጽ የጀመርነውን ጥረት ወደ ተግባር ለመለወጥ አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥር ነው።

ይህን አጋጣሚ በአግባቡ በመጠቀም ታሪካዊ ጠላቶቻችንን ጨምሮ ለሀገራችን በጎ ሃሳብ የሌላቸውን ግለሰቦች ፣ቡድኖችና ተቋማት ሀገር የማፍረስ ሴራ ልናከሽፍ ፤ ለዚህ የሚሆን ልበ ሰፊነት፣ አስተዋይነትና አርቆ አሳቢነት ልንላበስ ይገባል።



# "የሠላሙ ሁኔታ ይበልጥ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በትግራይ የሚገኘው ሕዝብም የእኛው ሕዝብ ነው ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፤ በአገራዊ የምክክር ሂደቱ ውስጥ ሕዝቡም ተሳታፊ እንዲሆንና ሃሳቡን እንዲያቀርብ አስፈላጊው ጥረት ይከናወናል ሲሉ አስረድተዋል።

የምክክሩ ሂደት በዋነኛነት አካታች ሆኖ እንዲከናወን ጽኑ ፍላጎት አለ፤ ለዚህም በትግራይ ክልልና ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ከሚገኙ ዜጎች ጋር የውይይቱን ዝግጅት ሂደት ማከናወን አስፈላጊ ስለሆነ ለዚህም ተዘጋጅተናል ብለዋል።

በአገራዊ ምክክሩ መሠረት መላው ኢትዮጵያውያን ልዩነትን በፈጠሩ ጉዳዮቻቸው ላይ በሰለጠነ መንገድ የሚወያዩበት አጋጣሚ ይፈጠራል። ለዚህ በጎ ሀሳብ እንዲሳካ ደግሞ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ የተለያዩ ዝግጅቶችን እያደረገ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

በዝግጅት ሂደቱ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን አባላት በተለያዩ ክልሎች ከሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር ውይይት እያደረጉ መሆኑን ጠቁመዋል።

በአሁኑ ወቅት ከአማራ ክልል የህብረተሰብ ክፍሎችና አስተዳደር አካላት ጋር በአገራዊ የምክክር ጉዳዮችና የተሳታፊ ልየታ ላይ በስፋት እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል።

የዞንና የወረዳ አስተዳደርን ጨምሮ ከሃይማኖት አባቶች የወጣትና ሴት ማህበራት ጋር አስፈላጊው ውይይት በማድረግ ለተሳታፊዎች ልየታ የሚረዱ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል ብለዋል።

በቀጣይ ውይይት ባልተደረገባቸው ኦሮሚያና የደቡብ ምዕራብ ክልሎች ላይ በተመሳሳይ አስፈላጊ ውይይት ከአስተዳደር አመራሮችና ከሕዝቡ ጋር ይከናወናል ሲሉ ተናግረዋል።

በአጠቃላይ ከአስተዳደርና የሕዝብ አካላት ጋር የሚደረገው ውይይቱ ካለቀ በኋላ የአጀንዳ መረጣና የተሳታፊ ልየታ ስራው ሲጠናቀቅ ለቀጣዩ ትውልድ ጭምር መሰረት የሚጥለው የአገራዊ ምክክር አጀንዳ የተለየባቸው ስብሰባዎች ይከናወናሉ ብለዋል።

በእስካሁኑ ሂደት ከተለያዩ ክልል ከሚገኙ የአስተዳደር አካላትና ማህበረሰቡ ጋር የተከናወኑ ውይይቶች በመልካምና ፈጣን ሁኔታ የተካሄዱ መሆናቸውን ኮሚሽኑ አስታውቋል።

በቀጣይም የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ቀጣይ ስራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ የሚመለከታቸው አካላትና ሕዝቡ የጀመሩትን ጥረት አጠናክረው እንዲቀጥሉ ፕሮፌሰር መስፍን ዓርአያ ጥሪ አቅርበዋል።

# በመዲናዋ በያዝነው ወር መጨረሻ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሁለት ሚሊዮን መጽሐፍት ታትመው መሰራጨታቸውንም ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በከተማ አስተዳደሩ በ2015 የትምህርት ዘመን በቅድመ አንደኛ ደረጃ የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የሙከራ ትግበራ የተደረገ ሲሆን፣ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ባሉ የትምህርት ደረጃዎች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡



አቶ አድማሱ ደቻሳ

ሥርዓተ ትምህርቱ ከመተግበሩ አስቀድሞ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ሲሠሩ እንደነበር ያስታወሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ከእነዚህ ሥራዎች አንዱ የመጽሐፍት ዝግጅት ነበር፡፡ በመሆኑም የመጻሕፍት ዝግጅት በአገር አቀፍ ደረጃ ከተሠራው ሥራ ጋር ይገናኛል ወይ የሚለውን የመገምገም ሥራ ከተሠራ በኋላ ወደ ሕትመት እንዲገባ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

ባለፈው ዓመት በ44 ትምህርት ቤቶች ላይ በሙከራ ደረጃ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ተግባራዊ መደረጉን ጠቅሰው፤ በሙከራ ትግበራ ወቅት የተገኙ ግብአቶችም በመጽሐፍት ሕትመቱ እንዲካተቱ ተደርጓል ብለዋል፡፡

ወደ ትግበራ ሲገባ የመጽሐፍት ዝግጅት ተጠናቆ ወደ ሕትመት እየተገባ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሙሉ በሙሉ ታትመው ማሰራጨት ባይቻልም በሶፍት ኮፒ ለሁሉም ትምህርት ቤቶች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ ከ31 ሺ በላይ የሚሆኑ መምህራንም ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር ትውውቅ አድርገዋል ብለዋል፡፡

በከተማ ደረጃ ሦስት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን መጽሐፍት ታትመው እንዲሠራጩ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዚህ ውስጥ ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ የመምህራን መምሪያ የተማሪ መማሪያ መጻሕፍት ታትመው ለትምህርት ቤቶች ተሠራጭተዋል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

መጽሐፍቱ እየታተሙ ከስር ከስር ለትምህርት ቤቶች እንዲደርሱ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በሂደት ላይ ትምህርት ቤቶች ለማስተማር ችግር እንዳይገጥማቸው የመጽሐፍቱ ሶፍት ኮፒ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ በያዝነው ወር መጨረሻ የመጽሐፍቱ ሕትመት ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ለትምህርት ቤቶች ለማሰራጨት እየተሠራ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

አንዳንድ የግል ትምህርት ተቋማት አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት በትክክል በመተግበር በኩል ክፍተት መስተዋሉን ያስታወሱት አቶ አድማሱ፤ ማስተካከያ እንዲያደርጉ በደብዳቤ በማሳሰብና ተነጋግሮ በመግባባት ሥራ እንዲሰሩ መደረጉን ጠቁመዋል፡፡

አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት ለመተግበር በሚደረገው ጥረት ውስጥ ሁሉም ነገር በአንድ ጊዜ ላይሟላ እንደሚችል ገልጸው፤ መጽሐፍቱ ላይም አልፎ አልፎ የሚነሱ አስተያየቶች ስላሉ ይህንን አስተካክሎ መሄድ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው ብለዋል፡፡

በመሆኑም በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይም ሆነ በመጽሐፍቱ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ካሉ ቢሮው ለማስተካከል ዝግጁ መሆኑን በመጠቆም ማንኛውም ሰው ጥያቄውን ማቅረብ እንደሚችል ጨምረው ገልጸዋል፡፡

# የኢትዮጵያ የውስጥ ችግር መፈታት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደሚያስችላት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ ዶክተር ዮናስ አሸኔ ገለጹ። ኢትዮጵያውያን ሠላም ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ርብርብ ማድረግ እንዳለባቸውም ጠቁመዋል።

ዶክተር ዮናስ አሸኔ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በጂኦ ፖለቲካ እሳቤ ውስጥ ከሁሉም የአፍሪካ ቀንድ አገሮች ጋር የምትዋሰንና ከመቶ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያለት ግዙፍ አገር ናት። በመሆኑም የሠላም ስምምነቱ ከዳር ደርሶ የውስጥ ችግሯን ከቀረፈች በቀጣናው ብሎም በአህጉር ደረጃ የሚጠበቅባትን የመሪነት ሚና እንድትወጣ ያስችላታል።

ኢትዮጵያ ሠላም ሲርቃት ችግሩ ለቀጣናውና ብሎም ለአፍሪካ እንደ አህጉር የሚተርፍ ነው ያሉት ዶክተር ዮናስ፤ ወረቀት ላይ የሰፈረው የሰላም ስምምነት ወደ ተግባር ተለውጦ የሚጠበቅባትን ቀጣናውንም ሆነ አህጉሪቱን የመምራት ታሪካዊ ቁመና ላይ እንድትገኝ ጠንካራ ሥራና የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ቁርጠኝነት እንደሚጠይቅ ተናግረዋል።

ጦርነቱ በአገር ላይ ሰፊ ጉዳት አስከትሏል ያሉት ዶክተር ዮናስ፤ እንደ ሕዝብ ያለንን ማህበራዊ ግንኙነት አጠናክረን በጋራ ለመቆም ከግጭት ቆስቋሽ ስሜት በመውጣት ሠላም ግንባታ ላይ ማተኮር እንደሚገባም ጠቁመዋል።

ፖለቲከኞቹ በሰላም ንግግር ስምምነት ላይ በመድረስ የሚጠበቅባቸውን የመሪነት ሚና ተወጥተዋል ያሉት ምሁሩ፤ ለስምምነቱ ስኬት ማህበረሰቡ ትልቅ ሚና እንዳለው በመረዳት እርስ በርስ ይቅር መባባል፣ የሞቱ ሰዎችን ማሰብ፣ ጉዳት የደረሰባቸውን መጠየቅ፣ በጦርነቱ የወደሙ አካባቢዎችን መልሶ መገንባት፣ ጦርነቱ ካደረሰብን የስነልቦና ጫና ለመውጣት መሥራትና የሠላም ግንባታ ንቅናቄ በማድረግ ኃላፊነታችንን ልንወጣ ያስፈልጋል ብለዋል።

ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለሰላም መረጋገጥና ለመልሶ ግንባታ ሥራዎች ላይ ርብርብ በማድረግ ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ ትልቅ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አስገንዝበዋል።

ዳግመኛ ልዩነቶች ሲፈጠሩም ወደ ጦርነት ከመሄድ ይልቅ ችግሮች በሠላማዊ መንገድ እንዲፈቱ መስራት እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ምሁራን፣ ሚዲያዎችና ማህበረሰቡም ሠላምን አዘውትረው በመስበክ የየድርሻውን ሚና ማበርከት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

በጦርነት የተጎዱ ዜጎችን ለማገዝ የሰብዓዊ እርዳታ ሥራዎችን በቴሌ በኩል በሚመቻች መንገድም ሆነ ሌሎች የሚፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎችን በመጠቀም ሁሉም ዜጋ በንቃት መሳተፍ እንደሚገባው አመልክተዋል።

# በኢትዮጵያ የ‹‹ምናባዊ ገንዘብ››...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አሠራር ተግባራዊ እያደረጉ ነው። በኢትዮጵያም የዚህን ገንዘብ ባህሪ ያገናዘበ የሕግ ማዕቀፍ ያስፈልጋል።

ምናባዊ ገንዘብ ግብይት በኢትዮጵያ ቢፈቀድና ባይፈቀድ ምን ጥቅምና ጉዳት አለው የሚለውን ለማወቅ የተጋላጭነት ጥናት እየተካሄደ ነው ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ የዓለም ባንክም በዚህ ረገድ ቴክኒካዊ ድጋፍ እየሰጠ ነው። የሚመለከታቸው የህግ አስከባሪ ተቋማትና ብሄራዊ ባንክን ጨምሮ ያሉበት የጥናት ቡድን በማቋቋም ጥናቶች እየተካሄዱ መሆኑን ገልጸዋል።

ይህ ጉዳይ በኢትዮጵያ ላይ በምን ዓይነት ሁኔታ እየተካሄደ ነው ጉዳቱ ምንድን ነው፤ ያለበትን ነባራዊ ሁኔታስ ምን ይመስላል? ለሚለውም ብሎም ከዚህም በመነሳት ተቋማዊና የህግ ማዕቀፎች ምን መምሰል አለባቸው የሚለውንም ጭምር የጥናቱ ውጤት የሚያሳየን ስለሚሆን ይህንንም በአግባቡ ተገንዝበን ወደ ህገ ወጥነት እንዳይሄድ የሚቆጣጠር ተቋም እንደሚያስፈልግ አብራርተዋል።

እስካሁን ድረስ ባለው ሁኔታ የፋይናንስ ሥርዓት ህግ መሠረት የኢትዮጵያ ብቸኛው መገበያያ ገንዘብ የኢትዮጵያ ብር ብቻ መሆኑን አመልክተው፤ከዚህ ውጭ ያለ ማንኛውም ግብይት ህገ ወጥ ነው፤ በአሁኑ ወቅትም በምናባዊ ገንዘብ ኢትዮጵያ ውስጥ ግብይት መፈፀም ወንጀል ነው። መሰል እንቅስቃሴዎችን ስናስተውል በብሄራዊ ባንክ በኩል ህገ ወጥ ስለመሆኑ ለህብረተሰቡ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን መንግስትም መግለጫ እየሰጠበት መሆኑን ተናግረዋል።

የውጭ ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ሥራ የሚጀምሩበት ዕድል ከተፈጠረም እነዚህ የፋይናንስ ተቋማት ከተለመደው ወጣ ያሉ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘው ሊመጡ እንደሚችሉ አብራርተዋል። እነዚህ ተቋማት የየራሳቸው ባህሪ ያላቸው ሲሆን ትስስራቸው ዓለም አቀፋዊና ቅርንጫፎቻቸው ከሀገር ውጭ ሊኖሩ ይችላል። በዚህ ረገድ የእነዚህን አካላት እንቅስቃሴ መከታተልና መቆጣጠር የሚያስችል ሁኔታ ስለመኖሩ በመንግስት ደረጃ የህግ ማዕቀፍ የዝግጅት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አቶ ብሌን አስገንዝበዋል።

እንደ አቶ ብሌን ማብራሪያ፤ በዋናነት ይህን የሚቆጣጠረው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የራሱን ህጎች ያወጣል። ከፋይናንስ ወንጀሎች አኳያ ደግሞ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት የራሱን ህግ ማዘጋጀት ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ በቂ ዝግጅት ለማድረግ የሚያስችል ሥራ ተጀምሯል። የልምድ ልውውጦችን ማካሄድ፣ ጥናቶችን ማከናወንና የመሳሰሉ ሥራዎችን ከወዲሁ መጀመራቸውን ገልፀዋል።

የትኞቹ ባንኮች ይምጡ ምን ያህል በሀገር ውስጥ ይስሩ የሚለው ነገር ከወዲሁ የሚታወቅ አለመሆኑን የተናገሩት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ አስቀድሞ ተቋማዊ ዝግጅት ማድረግ እንደ መንግስት አስፈላጊ በመሆኑ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ እየሠራበት ያለው እንደተጠበቀ ሆኖ በፋይናንስ ደህንነት አገልግሎትም በኩልም ዝግጅት የማድረግና ሁኔታዎችን የማጤን ጅምር መኖሩን አረጋግጠዋል።

# እኛና ያኛው ትውልድ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ዛሬ ስለ እኛና ስለዛኛው ትውልድ እናወራለን። ለመሆኑ ያኛው ትውልድ ማነው? ያኛው ትውልድ ከዚህኛው ትውልድ በምን ይለያል? ያኛው ትውልድ ኢትዮጵያን የሰራ የኢትዮጵያዊነት ድርና ማግ ነው። እኛን ያቆመን፣ ለእኛ ታሪክና ነጻነትን የሰጠ ባለማዕረግ ትውልድ ነው። ያኛው ትውልድ በሚደነቅ ባህል፣ በሚደነቅ አብሮነት የምትደነቅ ሀገር የሰራ የእውቀትና የጥበብ ባለቤት ነው።

በደሙ ሀገር ያቆመ፣ በአጥንቱ የነጻነት ቤት የሰራ እርሱ ነው..ያኛው ትውልድ። ያኛው ትውልድ በእኔና በእናንተ ልብ ውስጥ ታሪክ ያስቀመጠ፣ ስርዓት ያበጀ የማንነታችን ዋልታና ማገር ነው። ዛሬ ብቻ አይደለም፣ ነገ ብቻ አይደለም፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እስካሉ ድረስ ሁሌም የሚታወስ የሀገርና ህዝብ የትውልድም ጌጥ ነው።

ያኛው ትውልድ ከዓለም በፊት ገኖ፣ ከፍጥረት በፊት ሰልጥኖ እኔና እናንተን በጥበብና በስልጣኔ ከፊት ያስቀደመ ባለውለታ ትውልድ ነው። እርሱ በማይጠፋና በማይደበዝዝ እውነት ለዛሬ ማንነታችን ምሰሶ ነው። ከአጥንቱ ወጋግራ ከደሙ እያጠቀሰ ሀገር የሰራ፣ ህዝብ የፈጠረ ባላደራ ትውልድ ነው።

ከላቦቱ ኩሬ ከወዙ እያጠቀሰ እኔና እናንተን ያበጀ፣ ለእኔና ለእናንተ ታሪክና ትውፊት የተወ የሚደነቅ ትውልድ ነው። እኔነትን ሽሮ እኛነትን ያጸደቀ፣ ብሔርተኝነትን ተጸይፎ ኢትዮጵያዊነትን የተከለ አራዳ ትውልድ ነው። በአንድነትና በአብሮነት የተደነቀ የእያንዳንዳችን የኩራት ምንጭ ነው።

ያኛው ትውልድ በብሄርና በሃይማኖት መለያየትን ሳያውቅ በአንድ ታላቅ ስም በኢትዮጵያዊነት የቆመ፣ በሀገሩና በርስቱ ለመጡበት ቀልድ የማያውቅ ደግ አዛኝ ፈርሃ እግዚአብሔር ውስጡ ያደረበት ትውልድ ነበር። ያኛው ትውልድ በብዙ ነገሯ የምትደነቀውን የኩራት፣ የጽናት፣ የነጻነት ተምሳሌት የሆነችውን ሀገረ ኢትዮጵያ የሰጠን ባለውለታችን ነው።

እየተራበ ያጠገበን፣ እየተጠማ ከወይን የጣፈጠ የላቡን ወዝ እንጥፍጣፊ ታላቅ ሀገርና ህዝብ የሰጠን እርሱ ነው። ሳይማር ለዘመናዊው ዓለም መደነቂያ የሆነ ስልጣኔን የሰጠን፣ ለሰው ልጅ ሁሉ ተንግርት የሆኑ አክሱምና ላሊበላን የፈለፈሉ እጆች ባለቤት ነው። ሳይለብስና ሳያጌጥ ኩታና ካባ ያለበሰን፣ ከአንደበቱ ነውር የማይወጣ፣ ከእሱ በፊት በነበሩ በአባቶቹ ህግና ስርዓት ወጥቶ የሚገባ ትውልድ ነው።

ከዓለም በፊት፣ ከሰው ልጅ በፊት፣ ከስልጣኔ በፊት ራሱን በህግና ስርዓት የሚያስተዳድር በኩረ ጥበብ ባለቤት ነበር። ዛሬ ላይ እንደ ሀገር የምንኮራባቸው፣ እንደሀገር ያቆሙን፣ እንደታሪክ ቀና ያልንባቸው እንቁዎቻችን የነሱ የጥበብ ውጤቶች ናቸው። ዛሬ ላይ በዓለም ላይ የታወቅንባቸው፣ በዓለም ላይ ታላቅ የሆንባቸው ትውፊቶቻችን የዛኛው ትውልድ የአብራክ ክፋዮች ናቸው።

ዛሬ ላይ ነጻና ኩሩ፣ ጽኑና አይበገሬ ሆነን በአፍሪካና በዓለም ላይ ከፍ ያልነው በነሱ ነው። ዛሬ ላይ እንደ ሀገር ባለታሪክ፣ እንደ ህዝብ ባለማዕረግ ሆነን የቆምነው በነዛ ትጉ ነፍሶች ነው። ዛሬ ላይ ለአፍሪካና ለመላው ጥቁር ህዝብ የነጻነትና የቀና ማለት ፋና ወጊዎች ሆነን የምንታየው በእርሱ ነው.. በዛኛው ትውልድ...በአባቶቻችን።

እኛስ የዛሬዎቹ ምን አይነቶች ነን? እኛ የዛሬዎቹ እንደ አባቶቻችን የሆነ ምንም ነገር የለንም። እስካሁን ድረስ ያኛው ትውልድ በሰጠን እውነት ላይ የቆምን ነን። ለራሳችንም ሆነ ለሚመጣው ትውልድ የሚሆን አዲስ እውነት፣ አዲስ ታሪክ አዲስ ሀገር እየሰራን አይደለም።

አይደለም አዲስ ታሪክ ልንጽፍ ቀርቶ አባቶቻችን በነፍሳቸው ተወራርደው የሰጡንን እውነት እንኳን ውሸት ነው እያልን ነው። አይደለም አዲስ ታሪክ ልንጽፍ ቀርቶ ያኛውን ትውልድ በላቡ ወዝ ሞቶና ተጎሳቁሎ የጻፈልንን የምንወቅስ ወቃሽ ትውልድ ወጥቶናል። አይደለም አዲስ ሀገር ልንፈጥር ቀርቶ በብሔር ስም የአባቶቻችንን የነጻነትና የአደራ ምድር ለማፍረስ መዶሻ እያነሳን ነው።

ተምረን እንዳልተማርን አውቀን እንዳላወቀ መሆን መገለጫችን ሆኗል። ድሮነትን ተጸይፈን “አራዳ” ነን ባይ “ፋራዎች” ሆነን እየኖርን ነው። ነፍሳችንን ያለመለመ የዛኛው ትውልድ አሻራ መልካችን ላይ የለም። ምናችንም አባቶቻችንን አይመስልም። ተምረናል ግን አናውቅም። ሰልጥነናል ግን እንደ መሀይም ነን።

ስልጡን ዘመን ላይ ነን ግን ኋላ ቀሮች ነን። የአባቶቻችን ልጆች ነን ግን እንደ አባቶቻችን አይደለንም። በስርዓት በኢትዮጵያዊያን ወግና ባህል ያደግን ነን ግን ባለጌዎች ነን። ከዓለም በፊት ጠቢብ ነበርን ግን ምንም የለንም። አባቶቻችን ፈጣሪን የሚፈሩ፣ ለሰው ልጅ ሁሉ ሩህሩህ ነበሩ እኛ ግን ጨካኝ ወጥቶናል። ፈጣሪን አንፈራም። ፍቅርን ገለን ቀብረንዋል። አንድነትን ትተን መለያየትን የሙጥኝ ብለናል።

አባቶቻችን እንዲህ አልነበሩም..እነሱ የእውነት ሰው ነበሩ። እነሱ የእውነት ዜጋ ነበሩ። በሞታቸው እኔና እናንተን ፈጥረዋል። በጉስቁልናቸው ኢትዮጵያ የምትባል የነጻነት ምድር መስርተዋል። በሞታቸው ለጥቁሮች ሁሉ ተስፋ የሆነችን አንዲት ድንቅ ሀገርን ሰርተዋል። በአንድነታቸው ዓለምን ያስደነቀ ጀብድ ሰርተዋል። እኛ ግን ምናችንም እነሱን አይመስልም።

ከህግና ስርዓታቸው አፈንግጠን እርስ በእርስ መገፋፋትን ስልጣኔ አድርገነዋል። ከእውነታቸው ሸሽተን ነውረኛ ሆነናል። አደራቸውን ከማክበር ይልቅ አደራ በል መሆንን መርጠናል። ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ብሔርተኝነትን መርጠናል። ጀግንነትና፣ ሀገር ወዳድነታቸውን አልተላበስንም። ፍቅራቸውን፣ አንድነታቸውን፣ መተሳሰባቸውን አቀዝቅዘናል።

አብሮ መብላት፣ አብሮ መጠጣት ኋላቀር እስኪመስለን ድረስ የብቻ ሕይወትን የሙጥኝ ብለናል። ብዙዎች የሞቱላትን ሀገር እየተውን መሰደድ፣ የራስን ንቆ የባዕድ ሀገርን ማድነቅ ባህሪያችን ሆኗል። ከባህላችን ርቀን፣ ከማንነታችን ሸሽተን ሌላ ባዕድ ማንነትን ተላብሰናል። ታላቅ ሀገርና ህዝብ እንፈጥር ዘንድ እንደ አባቶቻችን መሆን አለብን። የአባቶቻችንን አይነት አእምሮና ልብ የእኛ ማድረግ ግድ ይለናል። አርነት ያወጣንን የአባቶቻችንን መንፈስ ፈልጎ ማግኘት ግድ ይለናል። ያኛውን ትውልድ ማወቅና መረዳት አለብን። ምክንያቱም ያኛው ትውልድ የታሪካችን፣ የባህላችን፣ የማንነታችን መብቀያ ለም መሬት ነውና።

ያኛው ትውልድ ጌጣችን ነው። አልቦ አሸክታባችን። የኔና የእናንተ ነፍስ ያጌጠችው በዚያ ትውልድ ጌጠኛ አልቦ ነው። የተሰፋነው፣ ሰው የሆነው በዚያ ትውልድ መልከኛ መርፌና ክር ነው። ያኛው ትውልድ ኩታና ቡሉኮ፣ እጀ ጠባብ፣ በርኖስ ኩታ፣ ተነፋነፍና አስኬማ ለብሶ ራሱን ሆኖ ራሱን መስሎ ነበር ታሪክ ያቆየልን እኛ የዛሬዎቹ የራሳችንን ንቀን ዘመናዊነት እየመሰለን የአውሮፓን ቀዳዳና ጨምዳዳ ድሪቶ እየሰበሰብን ራሳችንን እያጣን እንገኛለን።

ያኛው ትውልድ በባዶ እግሩ እየሄደ ለእኛ ጫማ ሰጥቶናል። የድሮዎቹ ደህና ዋልክ፣ ደህና ዋልሽ በማለት ከወገባቸው በማጎንበስ፣ ባርኔጣቸውን በማውለቅ ነበር በታላቅ ፍቅርና አክብሮት ኢትዮጵያዊነትን የሚገልጹት። እኛ የዛሬዎቹ የአባቶቻችንን ሰላምታ ቀይረን...ምኑንም በማናውቀው ፈረንጅኛ ሀይና --- ፒስ እየተባባልን ባህልና ወግ እንበርዛለን።

የድሮዎቹ ነውር ያውቁ ነበር..የድሮዎቹ ለፈጣሪ የተመቹ ነበሩ። የድሮዎቹ ተከብረው የሚፈሩ፣ ተወደው የሚከበሩ ነበሩ። የአሁኖቹ ነውር የማናውቅ ፈጣሪ የት እንዳለ የረሳን ግራ ገብቶን ግራ የምናጋባ ትውልድ ሆነናል። የድሮዎቹ እየፈተሉና ሸማ እየሰሩ፣ እየፎከሩና እየተመሰጋገኑ አንተ ትብስ አንተ በሚል ሀበሻዊ ወግና ስርዓት ተወልደው ያደጉ እንዲህም ነበሩ። እኛ የዛሬዎቹ መገፋፋትና እኔነትን የሙጥኝ ብለን ስር በሰደደ ትችትና ነቀፋ መኖርን የመረጥን ነን። ይቅርታና ፍቅር ስፍራቸው የት እንደሆነ አናውቀውም። ትዕግስትና በጎነት በእኛ ልብ ውስጥ ከሞቱ ቆይተዋል።

የድሮዎቹ ታሪክ እያጠኑ በአንድ ልብ፣ በአንድ መንፈስ ለጋራ ጥቅም ሲለፉ እኛ የዛሬዎቹ ግን በማንችስተርና በአርሴናል መከራችንን እናያለን። በማያገባን እየገባን፣ በሚያገባን ዝምታን እየመረጥን ለራሳችንም ለሀገርም ሳንሆን መሀል መንገድ ላይ የቀረን ሞልተናል። በታሪክ፣ በባህል በማይመስሉን ሀገራት ተጽእኖ ስር ወድቀን በምንም የማናገኘውን ድንቅ ኢትዮያዊነታችንን እያጣን ነው። የራሳችንን ጀግኖች ቸል ብለን በመሲና ሮናልዶ እየተወራረድን፣ በወለምታቸው እየታመምን፣ በሀዘናቸው እያዘንን እየተደባደብንና እየተፈነካከትንላቸው የቆምን ነን።

ዓድዋ ምንድነው? ስንባል ግራ የሚገባን፣ የአርበኞች ቀን መች እንደሚከበር ስንጠየቅ ቁጥር የሚምታታብን እኛ እኮ የከሰርን ትውልዶች ነን። ቫላንታይን ዴይና፣ ክሬዚ ዴይ መቼና ለስንተኛ ጊዜ እንደሚከበር ጠንቅቀን የምናውቅ፣ የሰማዕታትን ቀን ስንጠየቅ ግን የምንደናገር፣ አፕሪል ዘፉል መቼና የት፣ በማን እንደተጀመረ ስንጠየቅ በብዙ ማስረጃ የምንናገር ግን ደግሞ አቡነ ጴጥሮስ ማን እንደሆኑ ስንጠየቅ ግን ግራ የሚገባን እኛ እኮ ስልጡን አላዋቂዎች ነን።

የአውሮፓን ስልጣኔ፣ የኢሲያን ጓዳ ጎድጓዳ ስናውቅ የራሳችንን የረሳን፣ አጼ ምኒልክንና አብዲሳ አጋን የረሳን፣ ዘርዐይ ደረስንና ባሻ አውዓሎም የዘነጋን..በአባቶቻችን ሞት ቆመን ለገዳዮቻችን ነጭ የምናጎበድድ እኛ እኮ ብኩኖች ነን። እኛና የድሮዎቹ የተለያየን መልኮች ነን።

እንበረታ..እንጀግን ዘንድ የአባቶቻችን ሀቅ በነፍሳችን ላይ መብቀል አለበት። ድሮነትን መውረስ አለብን። ዓድዋን የፈጠረውን፣ በካራማራና በአንባላጌ ያሸበረቀውን የአንድነት ሸማ መልበስ አለብን። ድሮነት በእያንዳንዳችን ነፍስና ስጋ ላይ መዘራት አለበት። እውቀት ባልገባው፣ ስርዓት ባልጎበኘው ነፍስና ስጋችን ላይ የአባቶቻችንን ሀቅ ከትበን እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ ስንል በኩራት መናገር መልመድ አለብን።

እኛ ማንም የማይቀይረን የአባቶቻችን ልጆች ነን። እኛ ማንም የማይለውጠን የአባቶቻችን መልኮች ነን። እኛ ከራሳችን ውጭ የማንም የማንሆን የራሳችን ሰዎች ነን። ይሄንን እውነት ተረድተን እንደ አባቶቻችን ማሰብና፣ እንደ እነሱ መሆን ይጠበቅብናል። በየትኛውም መስፈርት ብንለካው የነሱ ሀሳብ፣ የእነሱ ህልም ከእኛ ሀሳብና ህልም በእጅጉ የተሻለ ነው። ዓድዋን የፈጠረው የነሱ የአንድነት መንፈስ ነው። ኢትዮጵያን የሰራው የእነሱ ፍቅርና ወንድማማችነት ነው።

እኛም በዛሬ ሕይወታችን ላይ ያለውን ድህነት፣ ያለውን ኋላቀርነት፣ ያለውን መጠላላት እናሸንፍ ዘንድ እንደ አባቶቻችን ያለ የጋራ መንፈስ ያስፈልገናል። ሀገራችንን ከድህነት፣ ህዝባችንን ከኋላቀርነት፣ እኛንም፣ ትውልዱንም ከወረረን የባዕድ አስተሳሰብ ነጻ እናወጣ ዘንድ ነጻ የሚያወጣን የአባቶቻችን የመቻል ትከሻ ያስፈልገናል። በቃ እነሱን መምሰል አለብን። ከዛሬ በኋላ በሚመጣው አዲሱ ቀናችን ላይ የአባቶቻችን ልጆች በመሆን ታሪክ መስራት አለብን።

ይሄኛው ትውልድ ያኛውን ትውልድ መምሰል አለበት። በእውቀት፣ በትህትና፣ በማጎንበስ መምሰል አለበት። በአስተሳሰብ፣ በመረዳት ያኛውን ትውልድ መምሰል አለበት። በመቻቻል፣ በመረዳዳት፣ በሀገር ፍቅር ስሜት አባቶቹን መሆን አለበት። በፍቅር፣ በይቅርታ፣ በትዕግስት የአባቶቹን ሰውነት መውረስ አለበት። አሁን ያለው የፖለቲካ ችግር፣ የኑሮ ውድነት እልባት የሚያገኘው ያጠለቅነውን የንቀት ጭንብል አውልቀን የአባቶቻችንን የመቻቻል ካባ ስንደርብ ነው።

ከዚህ ውጭ ወደፊት የመራመጃ አቋራጭ መንገድ የለንም። ከፍታችን ያለው በተውነውና በተጸየፍነው እኛነታችን ውስጥ ነው። ይሄኛው ትውልድ በጊዜው ላይ ጀግና መሆን ይጠበቅበታል። የሚመጣው ትውልድ ራሱን ፈልጎ የሚያገኘው በእኛ ውስጥ ነውና ለአዲሱ ትውልድ የሚሆን ኢትዮጵያዊ ሰውነት ያስፈልገናል።

ይሄ ሰውነት የሚገኘው ደግሞ በፍቅርና በእውነት ውስጥ ነው። በይቅርታና በመቻቻል ውስጥ ነው። በመነጋገርና በመስማማት ውስጥ ነው። ይሄ ሰውነት የሚገኘው እንደ አባቶቻችን የሆነ ልብ፣ የሆነ ነፍስ፣ የሆነ አእምሮ ሲኖረን ነው። ይሄ ሰውነት የሚገኘው እንደዛኛው ትውልድ እግዚአብሔርን ስንፈራ፣ ነውር ስናውቅ ነው። በጋራ ሀሳብ ሀገር ለመፍጠር በስርዓት የበቀልንባቸው የአባቶቻችን ነፍስ ግድ ይሉናል። በእኛ ውስጥ እነሱን እንፈልግ።

**የአውሮፓን ስልጣኔ፣ የኢሲያን ጓዳ ጎድጓዳ ስናውቅ የራሳችንን የረሳን፣ አጼ ምኒልክንና አብዲሳ አጋን የረሳን፣ ዘርዐይ ደረስንና ባሻ አውዓሉም የዘነጋን.. በአባቶቻችን ሞት ቆመን ለገዳዮቻችን ነጭ የምናጎበድድ እኛ እኮ ብኩኖች ነን። እኛና የድሮዎቹ የተለያየን መልኮች ነን**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ‹‹ውትድርና ለእኔ ጉልበቴም ስኬቴም ነው››

## - አቶ ሀብታሙ አበራ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

የሕይወት ስኬት እንደ ሙያ፣ እንደ ሰው ምልከታ፣ እንደ ሁኔታዎች አጋጣሚ የሚለካና የሚታይ ነው። ስኬት ለአንዳንድ ሰዎች በሙያ መደነቅና ዝነኛ ሆኖ መገኘት ሲሆን ፤ ለሌሎች ደግሞ ማወቅና ማማር ብቻ ይሆናል። ስኬትን በገንዘብ መጠን መመንደግ አድርገው የሚመለከቱም አሉ። ስለሆነም ሰዎች ለስኬት የሚሰጡት ትርጉም የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን። ይሁን እንጂ በስኬት እሳቤ የብዙ ሰዎችን ምልከታ የሚያቀራርበው ትርጉም አንድና አንድ ሲሆን፤ ይህም ደስተኛ መሆን ነው።

በሰው እይታ የሚሞላ ሀብት ንብረት ባይኖርም ደስታ ካለ ጉዞው ሁሉ ያማረ እንደሚሆን ሁላችንም እናምናለን። ምክንያቱም በደስታ ውስጥ ለሰው መትረፍ አለ። ሰውን ማትረፍ ደግሞ ስኬታማነትን በአንድ ጀንበር እንደማምጣት ነው። ለዚህ አብነት የሚሆኑን ለዛሬ ‹‹ የሕይወት ገጽታ›› አምድ እንግዳ ያደረግናቸው አቶ ሀብታሙ አበራ ሁነኛ ማሳያ ናቸው።

**የልጅነት ጊዜ**

ትውልዳቸው አዲስ አበባ ኮልፌ አጣና ተራ ልኳንዳ አካባቢ ነው። በቦታው ላይ እንደ ሌሎች ልጆች ቦርቀው አድገዋል ማለት ባይቻልም ቤተሰባቸውን እንዲያግዙበት እድል የሰጣቸው ስፍራ ስለሆነ የትውልድ ቦታቸውን አብዝተው ይወዱታል። በተለይም እናታቸውን ከማገዝ አኳያ ስፍራው ለእርሳቸው የተለየ ነበር።

አባት ወታደር በመሆናቸው ባለታሪካችን ልጅነታቸው ላይ ሳሉ እንደወጡ አልተመለሱም። አሁን ድረስ የት እንዳሉም አያውቁም። ስለዚህም እናታቸውን የማገዙ ኃላፊነት እርሳቸው ላይ ወድቆ ነው የቆየው። በእርግጥ እናታቸውም ብርቱ ሴት ነበሩ። ለልጆቻቸው ሲሉ የማይቆፍሩት ድንጋይ የለም።

እናታቸው እነርሱን ለማሳደግ አትክልት ሸጠዋል፤ ሸቀጣ ሸቀጦችን በጉልት መልክ ነግደዋል። የእለት ጉርሳቸውን ለመሙላት ሁልጊዜም እንደተሯሯጡ ነበር። ይህ ደግሞ ለትንሹ ሀብታሙ ራስ ምታት ነበርና እርሳቸውን ለማገዝ የማያደርገው ነገር አልነበረም። እናቱን ለመደጎም ሲል ከትምህርት ቤት መልስ ደብተሩን አስቀምጦ ሸንኮራ ንግድ ይሰራ ነበር። እንደ ልጅ ከረሜላ ሳያምረው ያገኛትን ገንዘብ በሙሉ ለእናቱ ይሰጣል።

እድሜው ከፍ ሲልም ሳይክል ገዝቶ በማከራየት በሚያገኛት እናቱን ያግዝ ነበር። ይህ ደግሞ ከዛሬው ህልሙ ጋር አገናኝቶታል። ማለትም ሳይክል ከማከራየት ባለፈ ሲበላሹ የመጠገን ሥራ ይሰራ ነበርና ቴክኒሽያን የመሆን ህልሙን እውን አድርጎበታል። ሀብታሙ ልጅነቱ አባት ከጎን ከሌለ መጀመሪያ ጫናው የሚያርፈው የመጀመሪያ ልጅ ላይ እንደሚያርፍ ያየበት ጊዜ ነው። ጭንቀቱ ሁሉ እናቱ ሆነው ለዓመታት ዘልቋል።

የትናንቱ ልጅ የዛሬው ጎልማሳ አቶ ሀብታሙ ልጅነታቸውን ሲያስቡ ቀድሞ ወደ አዕምሯቸው የሚመጣው የእናታቸው ልፋት ነው። የእርሳቸው እረፍት ማጣትም እንዲሁ ያስታውሱታል። ነገር ግን አይቆጩበትም። ምክንያቱም ትናንት ሥራን ባይለምዱ ኖሮ ዛሬን አያዩትም ነበር። በተለይ ደግሞ ሁልጊዜ የሚጓጉለትን የልጅነታቸውን ፍላጎት አያሳኩትም ነበር። ይህም ውትድርና ሲሆን፤ በእድገታቸው ውስጥ ልዩ ቦታ የሚሰጠው ነበር። ለዚህ ደግሞ መሰረት የሆናቸው በአካባቢው ያለው የውትድርና ማሰልጠኛ ተቋም ሲሆን፤ የወታደሮቹ አቋም፣ አለባበስና ስነምግባር እርሳቸውን ሁልጊዜ ይስባቸዋል። እናም በሙያው ለመሰማራት ይጓጉ ነበር። ቤተሰብ ሳያውቅም ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የገቡትም በዚህ ምክንያት እንደነበር ያስታውሳሉ።



ፎቶ በገባቦ ገብሬ

**በፈተና የታጠረው ትምህርት**

ትምህርትን አሀዱ ያሉት በዚያው በአጣና ተራ አካባቢ ነው። በቦታው ላይ ግን ብዙም አልቆዩም። ምክንያቱም ቤተሰብ ብዙ ፈተና ውስጥ ስለነበር ወደ ኬሚሴ እንዲጓዙ አድርጓቸዋል። እናም እስከ አምስተኛ ክፍልም ቢሆን እየተዟዟሩ ነው ያጠናቀቁት። ውትድርና ቤት አለመማር ቦታ የለውምና ከዚያ ቀጣዩ ትምህርት በርቀት ተምረው አጠናቀዋል። እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ተምረው ከጨረሱ በኋላም አሰላ ቴክኒክና ሙያ በመግባት በጀነራል መካኒክ የትምህርት መስክ መመረቅ ችለዋል።

አሁን ጀነራል መካኒክ ቢሆኑም አንድ ኢንጅነር የሚሰራውን ሙሉ እውቀት ኖሯቸው እያከናወኑ ይገኛሉ። በዚህም ‹‹ወረቀቱ ቢኖር በጣም ጥሩ ነው። ነገር ግን ጊዜ ስላልነበረኝና ልምዱን በየጊዜው በተለያየ መልኩ እያዳበርኩት ስለመጣሁ ትምህርቱን መማሩ አልቻልኩም። ብዙ የሚጨምርልኝ ነገር አለ ብዬ ለማሰብም ተቸግሬያለሁ›› ይላሉ።

እርሳቸው መማርን የሚያዩት ከወረቀት መኖር አንጻር ብቻ አይደለም። ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ገብቶ መውጣቱም ሊሆን አይችልም። መማር ዋጋው ከዚያ በላይ ነው። በተግባር የሚፈተን ሥራ ሲያርፍበት ነው ባይ ናቸው። ይህንን ደግሞ አሁን ላይ እያገኙት እንደሆነ ያስባሉ። በቋሚነት ገብተው ባይማሩም በሥራቸው የሁልጊዜ ተማሪ እንደሆኑም ያምናሉ። በምክንያትነት የሚያነሱት ደግሞ በየጊዜው የሚመጣውን ቴክኖሎጂ አውቀው መንቀሳቀስ መቻላቸውን ነው። በዚያ ላይ ገና ከዩኒቨርሲቲ የወጡ ተማሪዎችን ቀጥረው ሲያሰሩ ሁልጊዜ መምህራቸው ሆነው እንደቀጠሉ ነው። ስለሆነም ‹‹ትምህርትቤት ገብቶ ከመማር በላይ እየሆንኩ ስላለሁ መግባቱ አላስፈለገኝም›› ይላሉ።

እንግዳችን ትምህርት ቤት ገብተው ፤ የተለያዩ ስልጠናዎችን ሳይወስዱ በሥራቸው አጋጣሚ በርካታ ቋንቋዎችን ማወቅ ችለዋል። ለአብነት ከአገርኛው ብንነሳ ኦሮምኛ ፤ ትግሪኛ፤ ሱማልኛና አማርኛ በደንብ ከሚግባቡባቸው መካከል ናቸው። ከውጭው ደግሞ ቻይንኛና እንግሊዝኛ ጥሩ የሥራ ቋንቋቸው ሆነውላቸዋል። በተለያየ አጋጣሚ ወደተለያዩ አገሮች በመሄድም ልምዶችን መቅሰማቸው አንዱ ትምህርት እንደሆነም ይናገራሉ።

**የራስ ትግልና ውጤቱ**

‹‹ወታደር በመሆኔ ብዙ ነገር አግኝቻለሁ። አንዱ ከባድ ችግሮችን እንዴት ቀላል ማድረግ እንደምችል የተማርኩበት ነው። ከችግሮች እንዴት መውጣት እንደምችል አውቄበታለሁ። ፍርሃት ያደረበት፣ ግራ የተጋባ ወይም የተደናገጠ ሰው እንዳልሆንም አድርጎኛል። በጣም ጥንቁቅ እና መላ ፈጣሪ መሆንንም አስተምሮኛል። የበላይነትንና ጠንካራ ርምጃ መውሰድንም ልምድ ያደረኩበት ነው። ወሳኝነት ባህሪዬ እንዲሆንም አድርጎኛል። ሥራው ኃላፊነት የተሞላበትና አልፎ ተርፎ ውጤትን የሚያቀዳጅ ስለሆነ ድል እንዳለ እያሰብኩ እንድራመድም ያደረገኝ ነው።

የአካል ጥንካሬ እና ብቃትም ኖሮኝ ሰርቼው የማላውቀውን የጉልበት ሥራ ጭምር በውጤት እንዳከናውነው ያገዘኝ ነው። በማንኛውም መንገድ ችግር ቢገጥመኝ ስነ ልቦናዊ ጥንካሬ እንጂ ስነልቦናዊ ውድቀት እንዳይኖርብኝ አግዞኛል። ስለዚህም ሁልጊዜ እንኳንም ወታደር ሆንኩ እላለሁም›› ይላሉ ያሳለፉትን ጊዜ ከራስ የሥራ ፈጠራቸው ጋር አስተሳስረው ሲያስታውሱ።

እንግዳችን ሥራን ‹‹ሀሁ›› ብለው የጀመሩት ደብረዘይት ከተማ በሚገኘው ኢስት አፍሪካ በሚባል ድርጅት ውስጥ የቀን ሰራተኛ በመሆን ነው። ከውትድርናው ዓለም ወጥተው በገጠማቸው ምስቅልቅል ሕይወት የተቀላቀሉት ሥራ ነው። ስርዓቱ ሲገፋቸው ቀን ሥራ እሰራለሁ እኖራለሁ በማለት ነበርም ወደ ደብረዘይት የመጡት። ከዚያም በቻሉት ልክ በቦታው ዞር ዞር እያሉ እንዲያሰሯቸው የተለያዩ አካላትን ጠየቁ።

እንዳሰቡትም አንድና ሁለት ቦታ ላይ የቁፋሮ ሥራ ተሰጣቸው። ነገር ግን ከሳምንት በላይ በቦታው መቆየት አልቻሉም። ምክንያቱም የቀን ሥራ በባህሪው ሳይበሉ የሚሰራ አይደለም። እናም ሥራው አቃታቸውና ተባረሩ። ነገር ግን ወታደር ተስፋ መቁረጥን አያውቅምና ሌላ ሥራ ማማተራቸውን ቀጠሉ። የሞከሩትም ተሳካላቸው። ይህም ሥራ የጀመሩበት ኢስት አፍሪካ ድርጅት ውስጥ ሲሆን፤ ብቃትና ጥንካሬያቸውን ያሳዩበት ሆኗል። ይህንን ያዩ አለቆች በተለይም አቶ ቴዎድሮስ የሚባሉ ኃላፊ አስጠርተው ጠየቋቸውና የሙያ እድገት ሰጧቸው።

ከዚህ በፊት ምን ሙያ እንደነበራቸው ሲጠየቁም ኮንትሮባንድ ላይ እንደሚሰሩ ነገር ግን እንደከሰሩ ተናግረው እንደነበር የሚያስታውሱት ባለታሪካችን፤ ይህንን ያደረጉበት ምክንያት በነበረው ስርዓት በመገፋታቸው ሳቢያ ከውትድርና ስራቸው ስርዓቱን ተቃውመው ስለወጡ ታስረው እንዳይወሰዱ ወይም እንዳይገደሉ በማሰብ እንደሆነ ይናገራሉ። ውትድርናውን ትተው በመውጣታቸው ከራሳቸው አልፈው ቤተሰቦቻቸው መሰቃየታቸውን አይረሱትም። ይሁን እንጂ በስራቸው ስኬታማ ያደረጋቸው ወታደር በመሆናቸው እንደሆነ ያምናሉና ስቃያቸውን በደስተኝነታቸው ያጠፋፉታል።

አቶ ሀብታሙ በድርጅቱ ውስጥ ‹‹ከኬኒያ የሚመጣ ማሽን አለ እርሱን ትተክላለህ›› የመጀመሪያ የከፍታ ሥራ ትዕዛዛቸው ነበር። እንደተባሉት አደረጉም። ረዳት ኦፐሬተር በመሆንም ማገልገል ቀጠሉም። ብዙም ሳይቆዩ ሲኒየር ኦፐሬተር ሆኑ። ከዚያም አልፈው አለ የሚባለውን ሥራ በመካኒክነት አከናወኑ። በድርጅቱ ውስጥ አንቱታን ያተረፈላቸው ተግባርም ፈጸሙ። ለዚህ ደግሞ ያበቃቸው ወታደር መሆናቸው እንደሆነ ያነሳሉ።

‹‹ወታደር በባህሪው አልችለውም የሚለው ነገር የለም። በዚህም ከቀን ሥራው ወደ መካኒክነቱ ስገባ እንደምችለው አምኜ ነው። ውጤታማም ሆኜበታለሁ›› የሚሉት ባለታሪካችን፤ ውጤታማነት በአንድ ጀንበር እንደማይመጣ ያምናሉ። በዚህም መጀመሪያ የሥራውን ምንነት ተረድተው ለዚያ የሚመጥነውን ተግባር መከወን ጀመሩ። ከዚያም ለመማር ዝግጁ ሆነው የተሰጣቸውን በኃላፊነት መወጣት ቀጠሉ። ይህ ደግሞ በድርጅቱ ውስጥ ሰባት ዓመታትን ሲያሳልፉ በቂ እውቀትን ከመጨበጥ አልፈው ምስጉን ሰራተኛ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

አሁን በብዙ ልምድና ስልጠናዎች ራሳቸውን አዳብረው ወደ ራሳቸው ሥራ ዓለም ገብተዋል። እርሳቸው ቀጣሪ ጭምር በመሆንም ለሌሎች ልምዳቸውን እያጋሩም ነው። ስለዚህም ወደፊት ሊገጥሙዋቸው የሚችሉት ፈተናዎች ብዙም ሳያሳስቧቸው ያላቸውን ጊዜ በመያዝ እየተጓዙ ይገኛሉ።

**ሀብታሙ ዛሬ**

‹‹ሰራተኛ ሰው መቼም ቢሆን አይደክምም። የተሻለውን ሁልጊዜ ያያል። ›› የሚሉት እንግዳችን፤ ሰባት ዓመት የቆዩበትን ድርጅት ሲለቁ የተሻለ ቦታ ላይ ነበሩ፤ ደመወዝ ጨምረውላቸው እንዲቆዩም ለምነዋቸው እንደነበር አይረሱትም። ሆኖም

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ



ከፊት ያለውን የተሻለ ነገር የግድ ነውና ድርጅቱን እንዲለቁት ሆኑ። ከዚያ እንደወጡ በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ነው የመጡት። ቃሊቲ አካባቢ በሚገኘው ፋንሱን በሚባል የቻይና ካምፓኒ ማሽነሪ ሽያጭ ውስጥ።

ካምፓኒው ለሌላ ድርጅት አጠቃላይ ማሽነሪዎችን ሸጦት ነበርና የገዛው አካል እርሳቸውን በመካኒክነት ቀጥሮ ያሰራቸዋል። ቴክኒካል ኃላፊ በመሆንም እንዲሰሩ አድርጓቸዋል። በዚህ ሳያበቁ ሙሉ ለሙሉ ማሽነሪውን ተረክበው መስራታቸውን እንዲቀጥሉ ሆነዋል። ይህ ደግሞ የሆነው ከቻይናው ካምፓኒ ጋር ቀረቤታቸውን በማጠናከራቸው ነው። በአገር ደረጃ ውክልና በመውሰድ ሙሉ የማሽነሪ ሽያጩን እንዲያከናውኑ እድሉን ሰጥቷቸዋል። እናም አሁን ድረስ ድርጅቱን ቢለቁም ወኪልነቱ በእርሳቸው አማካኝነት የሚንቀሳቀስ ሆኗል። ተከላውንም ቢሆን ‹‹ሀዊ ኢንጂነሪንግ ፒኤልሲ›› የተሰኘ የራሳቸው የኢንጂነሪንግ ካምፓኒ ስላላቸው በእርሱ በኩል እድሉን ካገኙት ተግባሩን ይከውናሉ።

አቶ ሀብታሙ ሙያቸውን ለማሳደግ የተለያዩ አገራት በመሄድ ልምድ ቀስመዋል። አንዱ ቻይና እንደነበር ያነሳሉ። ከአንዴም ሁለትና ሦስት ጊዜ በመሄድ ማሽነሪዎችን በሚገባ የሚያውቁበትን ልምድ አካብተዋል። አሁን እንደ አገር በድርጅታቸው አማካኝነት እየተዘዋወሩ የሚሰሩትም ለዚህ ነው። ከሰሯቸው ሥራዎች መካከል ባህር ዳር ላይ ሦስት ፕሮጀክቶችን፤ ቃሊቲ ላይ አልባር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያን፤ በሐዋሳ የሚገኝ ሱፐር አባ የሚባል ድርጅትንና ደብረብርሃን ላይ የሰሩት የዘይት መጭመቂያ ፋብሪካና የእህል ማበጠሪያ ማሽን በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

እንግዳችን ከኢንጂነሪንጉ ሥራ ባለፈም የተለያዩ ሥራዎችን ሞክረዋል። እንደውም ‹‹ያልገባሁበት የሙያ መስክ የለም›› ይላሉ። ለአብነት ከአነሱልን መካከል የከብት እርባታ አንዱ ነው። ከብቶቹ ሲሞቱባቸው ነገሩን እርግፍ ቢያደርጉትም። ከዚያ የቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ በማህበር የሚደራጁበትን እድል ሲሰጣቸው እርሳቸው የቀድሞ መከላከያ ሰራዊት አባላትን በማሰባሰብ በስራ አስኪያጅነት ማህበሩን እየመሩ የመኪና ጋራዥ አገልግሎት መስጠት ጀምረውም ነበር። በዋናነት የቀለም ቅብና የቦዲ ሥራ ያከናውኑ ነበርም። ነገር ግን ይህም ለተወሰነ ዓመት ከሰሩ በኋላ በባህሪ መስማማት ስላልቻሉ ማህበሩ ፈረሰ።

አቶ ሀብታሙ በአንድ ጊዜ ሁለትና ሦስት ሥራን መስራት የሚወዱ በመሆናቸው ሥራቸው አልተቋረጠም። ምክንያቱም የቻይኖቹ ማሽነሪ ሽያጭ ስራ አለ። እናም አሁን ድርጅታቸው ሥራውን በዋናነት በማሽን ጥገና፤ ተከላና ሽያጭ ላይ አድርጎ ይንቀሳቀሳል። በቀጣይ ትልቅ ሕልምም አለው። ይህም ማሽነሪ ማምረት ሲሆን፤ የተወሰነ ክፍሉን በሁለት ዓመት ውስጥ ለማምረት ዝግጅት እያደረጉ ይገኛሉ። ለዚህ ደግሞ ቴክኖሎጂውን ሙሉ ለሙሉ ማወቃቸው እንደሚያግዛቸው ያምናሉ። በተጨማሪም አብረዋቸው የሚሰሩት ካምፓኒዎች ቴክኒካል ፓርቱን እንደሚያግዟቸው ቃል ስለገቡላቸው የእቅዳቸው ፍጻሜ ቅርብ እንደሚሆን ያስባሉ።

### የውትድርና ጥሪ

አቶ ሀብታሙ ገና በ14 ዓመታቸው ነው መከላከያን ተቀላቅለው ለአገራቸው የተዋደቁት። ወደዚህ ሙያ ሲገቡ ልጅ ስለነበሩ በቅርብ የሚከታተላቸው ሰው ነበር። መጀመሪያ ሥራቸው የሆነውም ከተወሰነ ስልጠና በኋላ እግረኛ ሆኖ ማገልገል ነው። ተግባሩን በሚፈለገው ደረጃ በመከወናቸው፤ ጠንካራና ቀልጣፋ በመሆናቸው ከዚያ ባሻገር የሚል ሥራ ተሰጥቷቸዋል። ይህም ኮሚኒኬሽን ዘርፉን በተለያየ ቦታ ላይ ሆነው እንዲያገለግሉ ነው።

‹‹ኮሚኒኬሽን የሰራዊቱ የጀርባ አጥንት ነው። ሕይወታቸውም እንደሆነ የሚታሰብ ክፍል ነው።›› የሚሉት አቶ ሀብታሙ፤ እዚህ ክፍል ሲመደቡ ትልቅ ኃላፊነት እንደተሰጣቸው በማሰብ በሄዱበት ሁሉ በትጋት ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ከውትድርናው እስኪለዩ ድረስም ኃላፊነታቸው ከፍ እያለ ይሂድ እንጂ ከዘርፉ አልወጡም ነበር።

አቶ ሀብታሙ ውትድርናው ሲቀላቀሉ እስከ አምስተኛ ክፍል ብቻ ተምረው ነው። ነገር ግን መማር ፍላጎታቸው ነበርና የውትድርናውን ዓለም በሚገባ እንዲያውቁት ሆነው ነው የወጡት። መውሰድ ያለባቸውንም የውትድርና ስልጠና ወስደዋል። መጀመሪያ የሰለጠኑበት ቦታ ጦላይ የወትድርና ማሰልጠኛ ሲሆን፤ ጥሩ አቅም የፈጠሩበት ነው። በመቀጠልም ወደ ደብረዘይት በመሄድ የተለያዩ ስልጠናዎችን ወስደዋል። ሦስተኛ የስልጠና ቦታቸው አዲስ አበባ ላይ ቃሊቲ አካባቢ የሚገኘው አየር መቋሚያ ምድብ ሲሆን፤ እስከ 1987 ዓ.ም መጨረሻ የቆዩበት ነው።

በውትድርና ዓለም ስልጠና ብቻ ሳይሆን ትግልም አብሮ የሚጓዝ ተግባር ነው። ስለዚህም ከስልጠናው ጎን ለጎን አገር መጠበቁና፤ ጸጥታ ማስከበሩን ሰርተውበታል። ትግራይ ክልል ሳይቀር ይህንን ተግባራቸውን ከውነዋል። ለምሳሌ፡- የሃ የምትባል ከተማ የውትድርና ሥራቸውን ከሰሩባቸው ቦታዎች መካከል ይጠቀሳል። በርሃሌ ከተማ ተዛውረው ግዳጃቸውን ተወጥተዋል። ይህ ደግሞ እስከ 1989 ዓ.ም አጋማሽ ድረስ የዘለቀ ነው። ቀጥለው ወደ ሱማሌ ክልል ነው የሄዱት። ምክንያቱም ጊዜው የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት የተጧጧፈበት ወቅት ነበር። እናም በቡሬ ግንባር ሆነው ውጊያው እስኪጠናቀቅ ድረስ የሻለቃ መገናኛ ኃላፊነትን በመያዝ ቆይተዋል።

ውጊያው ካለቀ በኋላ ደግሞ ወደ ድሬዳዋ ጉዟቸውን አድርገው ለተወሰነ ጊዜ አርፈዋል። ይሁን እንጂ በጊዜው ግምገማ ነበርና ውስትን የሚሰብር ነገር ገጥሟቸዋል። ከውትድርናው ዓለም እንዲለዩም ያደረጋቸው ይህ ተግባር ነበር። ግምገማው አድሎነት ብቻ ሳይሆን ማሸማቀቅ የነበረበት ነው። ዳግመኛ መከላከያ የሚባል ነገር እንዳይታሰብ የሚያደርግም ነው። ምክንያቱም ሹመቱ ወይም ምስጋናው በሥራ ሳይሆን በቅርበትና በተፈላጊነት የሚከወን ነበር። በዚህ ውስጥ ደግሞ ‹‹ለምን›› ማለትም አይቻልም። ይህ በመሆኑም የሰሩ ሰዎች ዓይንህ ለአፈር ተባሉ። እርሳቸውም አንዱ ነበሩና ይህንን እያየሁ አልቀመጥም በማለት ከመከላከያ ጠፍተው ሄዱ።

መጥፋታቸው ብዙ ነገራቸውን አደበላልቆባቸው ነበር። አንዱ ቤተሰቤን ማስቃየቱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የእርሳቸውን ሕይወት አዘቅት ውስጥ መክተቱ ነው። አንድ ቲሸርትና አንድ ሱሪ ብቻ ይዘውም እንዲሰደዱ አድርጓቸዋል። ነጻ ሆነው ለመሥራትም አልቻሉም፤ በሙያቸው ማገልገልም እንዲሁ። ስለዚህም እሰረዋለሁ ብለው ያላሰቡትን የቀን ስራ በመስራት ጊዜውን እንዲገፉ አስገድዷቸዋል። ከመከላከያ የወጡበት ዓመት ዋሽተው ጭምር እንዲቀጠሩ ያደረጋቸው ነው። ምክንያቱም ነገሩ ከመሞት መሰንበት ነው።

አንድ ነገር ግን ያምናሉ። መከላከያ ውስጥ በመግባታቸው ብዙ ነገር እንዳገኙ። አንዱ ወታደር ዝም ብሎ ሥራ ውስጥ አለመግባቱ ነው። ለሚሰራው ሥራ አላማ አለው፤ አቋምም ይይዛል፤ ፍርሃት የሚባልን ነገር አያስብም። ከዚያ ይልቅ ጥንቁቅነትን መመሪያው ያደርጋል። ለድርጊቱ ቀድሞ ማወቅ ያለበትን ነገር ይመረምራል። ስለዚህም ብር ሳይሆን ሕሊናውንና ክብሩን ያስቀድማል። ሁልጊዜ እዚህ ላይ እቆማለሁ ሳይሆን ታሪክ እሰራለሁ ብሎ የሚያምን ነው። ›› የሚለውን።

### ወታደር ለአገሩ

ወታደርነት መነሻውም ሆነ መዳረሻው አንድ ነገር ነው። የሀገር ፍቅርና የሀገር ክብር። ሀገሩ ካለች እርሱ ቢሰዋ እንኳን ቤተሰቡ እንደሚኖር ያምናል። የሰው ልጅ ጭምር ደስተኛ ሆኖ እንደሚቀጥል ያስባል። ስለዚህም እስከ መጨረሻው የሚሳሳላትን ሕይወቱን ለውድ ሀገሩ ሉዓላዊነትና ለሕዝቡ ሰላም አሳልፎ ይሰጣል። ለእርሱ ሀገሩ የደም ቃሉ ነችና የሚሰስተው ነገር አይኖርም። በታማኝነት ማገልገሉም ነው በክፉ ሰዎች ያስበላው። የአገሩን ሰው ልክ እንደራሱ ይወደዋል፤ ያገለግለዋልም።

### መልዕክት

ባለፉት አመታት በአገራችን ውስጥ እያየነው የመጣነው መከራ ከቀን ወደ ቀን እየከፋ ሲመጣ ቆይቶ አሁን የተስፋ ወጋገን መታየት ጀምሯል። የሰላም አየር በሀገራችን መንፈስ ጀምሯል። ኢትዮጵያን ተነጋገግረን ወደ ሰላም መምጣታችን ሁላችንንም ድል አድራጊዎች ያደርገናል። የማናሸንፈው ነገር የለምም። ስለሆነም ያንን አስበን እንደሕዝብ አንድነታችንን በማጠናከር አገራችንን ከአለችበት ችግር ማውጣት ይጠበቅብናል የመጀመሪያው ምክራቸው ነው። አንድ ከሆንን የሚጫነን ኃይል አይኖርም፤ ኢኮኖሚያዊ ችግር፣ ፖለቲካዊ ጫና እንዲሁም ስነልቦናዊ ውድቀት የሚባሉ ነገሮች አይነኩንም ይላሉም።

ሌላኛው መልዕክታቸው በአገራችን የነበሩ ችግሮች ወደፊት ላለው አንድነታችን ጭምር ጥላ የሚሆን ነው የሚለው ሲሆን፤ እንደ ዜጋ የፍቅር መንፈሱን፣ ልማዱንና የእለት ተእለት ተግባሩን፣ ከሃሳቡና ከስነምግባር መርሁ ጋር ለማስተካከልና ወደ ሰመረ ሕይወት ከፍ ለማድረግ ቀን በቀን በመታገል ሁላችንም የድርሻችንን እንወጣ። እኛ ወደ ባሰ መከራ ሳይሆን ወደተሻለው መውጣት ያለብን ሕዝቦች ነን። ቢወድቅ እንኳ ተነስቶ የሚያንሰራራ ምሉዕ፣ የስሜትና የመንፈስ ስምረት የሚያስፈልገን ነን። ስለሆነም እዚህ ላይ ከምንም በላይ መስራት ይኖርብናል ይላሉ።

አይቀሬ መዘዞችን እየጐነጐኑ ቁልቁል የሚጐትቱን፣ ወደ አይምሬ መቀመቅ ወርውሮ የሚፈጠፍጠንን አንቀበልም ማለት መጀመር ያለብን ከአሁኑ ነው የሚሉት አቶ ሀብታሙ፤ ለዚህ ደግሞ የሕይወት መንገዳችንን የሚያቃና፣ ከፍ ወዳለ ወደከበረ ሕይወት የሚመራን ሰው ያስፈልገናል። አሁን ይህ እንዳለን የሚያሳዩ በርካታ ነገሮች አሉ። ስለዚህም እርሱን መደገፍና ለተሻለች ኢትዮጵያ መትጋት ይገባናል ሌላው መልዕክታቸው ነው።

እኛ ከሚያጨልም ይልቅ የሚያፈካ፣ የተሳከረ ሳይሆን የተስተካከለ፣ የጠመመ ሳይሆን የተቃና የሚያደርገን ባህልና ታሪክ ያለን ሕዝቦች ነን። ሆኖም መጠቀሙ ላይ አልቻልንበትም። እናም ከክስረት ይልቅ የስኬት በረከትን ማብዛት ላይ ማተኮር ይኖርበናል። ያ ደግሞ ባህልና ታሪካችን ነውና እርሱን በሕይወት ልንኖረው ያስፈልጋል። ምክንያቱም እርሱ ከባዶ ድንዛዜ ይልቅ የሚያነቃ የሕይወት ጣዕም አለው። ከወረደ ይልቅ የከበረ መንፈስን የሚያላብስ ነው። ለድንቅ የሰው ተፈጥሮ የሚመጥን ሃሳብና ምኞትንም ይሰጠናል። ስለሆነም እርሱን ለብሰን ብርሃን ለአጡት ብርሃን እንሁናቸውም ባይ ናቸው።

ሃሳብና ተግባር፣ መንፈስና ስሜት፣ የስነ ምግባር መርህና ባሕርይ ሲጣጣም ትርጉሙ አንዱ የሕይወት ገፅታን ይሰጠናል። ይህም አገር ነው። ለዛሬዎቹ ኢትዮጵያዊያን ይህ ብቻ ያስፈልገናል። ስለሆነም ከውስጥም ከውጭም ያማርን እንድንሆን እነዚህ ባህሪያትን እንላበስ። ምክንያቱም እነሱ ካሉን የሚያደበዝዝ፣ የሚያጠወልግ ፍቅር ሳይሆን በአበቦች ወደ ተንቆጠቆጠ የደስታ መስክ እንወርዳለን። አዕምሯችን በደመቀ የደስታ እርካታ ውስጥ ይወድቃል። ከመልካም ውድ ስሜት ጋር የሰመረ፣ በጐ ክቡር ፍቅርን የሚያመነጭ ሰው እንሆናለንም። እናም ይህ ይገባናልና መመሪያችን እናድርገው ማሳረጊያ መልዕክታቸው ነው። እኛም ምክሩ ያሻግረናልና እንጠቀምበት በማለት ሀሳባችንን ቋጨን። ሰላም!!

አዲስ ዘመን | እሁድ ጥቅምት 27 ቀን 2015 ዓ.ም



# “አስተሳሰባችን ቀና የሚሆነው ካለንበት ሰፈር ለመውጣት ፍቃደኛ ስንሆን ነው”

## የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ዳዊት

**ዳግም ከበደ**



ኢትዮጵያ የአያሌ ቱሪስት መስህቦች ባለቤት ናት። የሰው ዘር መገኛ ይህች ሀገር፣ ከ3 ሚሊዮን ዓመታት በላይ እድሜ ያስቆጠረችው “የሉሲ” ወይም ድንቅነሽ ቅሬተ አካል፣ የአረቢካ ቡና ዝርያ ፣ የዓለማችን ረጅሙ ወንዝ ጥቁር አባይ ፣ የኤርታአሌ የእሳተ ገሞራ ፣ የዓለማችን እጅግ ረባዳና ሞቃት ስፍራ ዳሎል መገኛዎች መሆኗ በእጅጉ ይታወቃል።

በርካታ የስምጥ ሸለቆ ሃይቆችና ፍል ውኃዎች፣ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙትን ጨምሮ የአያሌ የዱር እንስሳት ፓርኮችና መጠበቂያዎች ይገኙባታል። በርካታ ባህሎች፣ ቋንቋዎችና የተለያዩ እምነቶች ሀገርም ናት። በርካታ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፣ ሰው ሰራሽና ባህላዊ ቅርሶችን በዩኔስኮ በማስመዝገብ በአፍሪካ ቀዳሚዋ አገር ለመሆን በቅታለች።

የእነዚህ ሁሉ የቱሪስት መስህቦች ባለቤት ብትሆንም ፣ በውጭ ሀገሮች ቱሪስቶች ካልሆነ በስተቀር በሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ብዙም ያልተጎበኘች እና በዜጎቿ ዘንድ የመጎብኘትና የማወቅ ባህል በሚፈለገው ልክ ያልዳበረባት ስለመሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ከሰሞኑ የቱሪዝም ሚኒስቴር “ልወቅሽ ኢትዮጵያ” የተሰኘ እና የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ማነቃቃት እና ማበረታታትን ያለመ ንቅናቄ መጀመሩን አስታውቋል። ንቅናቄው በዋናነት ትውልዱ ስለ ሀገሩ ባህልና ታሪክ በአጠቃላይ ቱሪዝም መዳረሻዎች እንዲያውቅ የሚያስችል መሆኑም ተጠቁሟል። ኢትዮጵያ የበርካታ የቱሪዝም መዳረሻ ሥፍራዎች ባለቤት መሆኗን ለትውልዱ በማስተዋወቅ ረገድ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ንቅናቄው ማስፈለጉ ተነግሯል። ይህንን ጉዳይ በማስመልከት የዝግጅት ክፍላችን ከቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ዳዊት ጋር ያደረገውን ቆይታ ይዘን ቀርበናል።

**አዲስ ዘመን፡- “ልወቅሽ ኢትዮጵያ” የተሰኘ ንቅናቄ በይፋ አስጀምራችኋል። ስለመሆኑ የዚህ ንቅናቄ ዋና አላማና መዳረሻ ግብ ምንድን ነው?**

**ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት፡-** ‹‹የልወቅሽ ኢትዮጵያ›› ዋና አላማ የአገር ወስጥ ቱሪዝምን ማነቃቃትና ማንቀሳቀስ ነው። የአገር ውስጥ ቱሪዝሙ ማለትም በአገራችን ያለውን ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ ተዘዋውሮ በጋራም ሆነ በተናጠል የመጎብኘት ባህል አሁን ካለው በተሻለ መልኩ ማደግ አለበት። አካባቢያችንንም ሆነ ራቅ ብለው የሚገኙትን ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ እና ሰው ሰራሽ የቱሪዝም መስህቦችን ማወቅ ያስፈልገናል።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ በጣም ትልቅ አገር ነች። በጣም ብዙ ታሪካዊ፣ ባህላዊ ቅርሶች እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብቶች አሏት። ህዝቦቿ ከአንድ ቦታ ወደሌላኛው ተንቀሳቅሰው ይህን ሀብት የሚያዩበት በዚህ ሀብት የሚዝናኑበት፣ ልምድ የሚወስዱበት በዚያው ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚገኝበት መሆን ይኖርበታል።

እንደሚታወቀው ቱሪዝም በዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ በቅርቡ ነው የተካተተው፤ አሁን እንደ ቁልፍ የኢኮኖሚ ዘርፍ ተወስዷል። የቱሪዝም መዳረሻዎችን ይበልጥ ሳቢ በማድረግ ኅብረተሰቡ ሀገሩን የማወቅ ጉጉት እንዲኖረው ለማድረግ እየተሠራ ነው። የሀገር ውስጥ ቱሪዝም የእርስ በርስ የባህል ትውውቅን በማጠናከር ሀገራዊ አንድነት እንዲጎለብት ሚናው የጎላ ይሆናል።

ንቅናቄው በዋናነት በትምህርት ቤቶች በሚመሠረቱ የቱሪዝም ክበባት እና በተቋማት አማካኝነት ይተገበራል። በተለይ ታዳጊዎች ነባሮቹን እና አዳዲሶቹን የቱሪስት መዳረሻዎች እንዲጎበኙ እና እንዲያውቁ ዕድል ይፈጥራል፤ በተጨማሪም የሆቴል እና ቱሪዝም ኢኮኖሚን በማነቃቃት ረገድም ከፍተኛ አበርክቶ እንዲኖረው ተፈልጎ ነው ንቅናቄው የተጀመረው።

**አዲስ ዘመን፡- ትውልዱ አገሩን እንዲያውቅ ከማስቻል ባለፈ ኢኮኖሚውን ያነቃቃል ብለዋል። ይሄ በምን መልኩ ይፈጸማል?**

**ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት፡-** በዋናነት የቱሪዝሙ ዘርፍ ባለፉት ሁለት አመታት በኮቪድ፣ በአገር ውስጥ ባለው የፀጥታ ችግር ምክንያት በጣም ተጎድቶ እና ተፋዝዞ ቆይቷል። ወረርሽኙ በዓለም ደረጃ ከባድ ቀውስ አስከትሏል። እኛ ከዚህ ለማንሰራራት በዋናነት በአንደኛ ደረጃ እንደ መነሻ አድርገን እየተጠቀምን ያለነው የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ማነቃቃትን ነው። ይህንን እንደ ስትራቴጂ አስቀምጠናል።

ሁለተኛው ደግሞ ከጎረቤት አገራት ያለውን ግንኙነት እንዲሁም ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ግንኙነቱን በማጠናከር እንዲሁም ዲጂታል ፕሮሞሽኑን በማጠናከር ላይ ያተኮረ ስትራቴጂ ነው። በዋናነት ግን የአገር ውስጥ ቱሪዝም በማጠናከር በዜጎች ዘንድ የመጎብኘትና የመንቀሳቀስ ባህል እንዲሰርፅ ብናደርግ የበለጠ ከቱሪዝም የሚገኘውን ጥቅም ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ይችላል።

በዚህ ምክንያት ነው በልወቅሽ ኢትዮጵያ ንቅናቄ የአገር ውስጥ ቱሪዝሙን ለማንቀሳቀስና ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማሳደግ በማለት ንቅናቄው ይፋ የተደረገው። ህዝባችን ብዙ ነው። በርካታ የሚጎበኙ መስህቦች አሉን። በዚህ ላይ ከሰራን ኢኮኖሚው ላይ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችል ጥቅም እናገኝበታለን” የሚል እሳቤ የያዘ ንቅናቄ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ንቅናቄ መቼ ይጀመራል? ምን አይነት ተግባራቶችስ ይካተቱበታል?**

**ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት፡-** አሁን ንቅናቄው ተጀምሯል። በውስጡ በርካታ ተግባራት አሉት። ከዚህ ውስጥ በዲጂታል ቅስቀሳ፣ ልዩ ልዩ ሁነቶችን በማካሄድ አላማውን የማስተዋወቅና ዜጎች ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እየሰራን ነው።

ከዚህ ውስጥ “የአገርህን እወቅ” የቱሪዝም ክለቦች ማለትም በሁሉም ትምህርት ቤቶች ያሉትን ተጠቅሞ ፅንሰ ሃሳቡን የማስተዋወቅ ስራዎች ይካሄዳሉ። በዚህም ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ድረስ ያሉት ይካተታሉ። ሁሉም ወጣቶችና ታዳጊዎች አገራቸውን ማወቅ እንዲችሉ ይህንን መዋቅር ለመጠቀም አስበናል።

በዚህ ሂደት ውስጥ በርካታ የጉብኝት መርሃ ግብሮችን በማቀናጀት ተማሪዎች የሚመለከቷቸውንና ሊያውቁ የሚገባቸውን የመስህብ ስፍራዎች የመለየት ስራ ጎን ለጎን ይሰራል። ክልሎች የከተማ አስተዳደሮችና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በዚህ ንቅናቄ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ እቅዶችን ነድፈን ወደ ስራ ገብተናል።

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ንቅናቄ ውስጣዊ አንድነትን የማጠናከር፣ የዜጎችን ማህበራዊና ፖለቲካዊ አንድነት የማጉላት ግብ አስቀምጣችኋል። ይህንንስ በምን መልኩ ልታሳኩት አሰባችሁ?**

**ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት፡-** ልወቅሽ ኢትዮጵያ በዋናነት ሊያስገነዝበን የሚፈልገው አገራችንን እንድናውቅ ነው። ከጫፍ ጫፍ ያለውን ህብረተሰባችንን ብናውቅ አንዳችን የአንዳችንን ስሜት የመረዳት ነገር ይፈጠራል።

ይህ ይዞት ከሚመጣው የመደጋገፍና የመረዳዳት ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ ባሻገር ፖለቲካዊና ማህበራዊ ፋይዳም አለው። ታሪካችን የሚያስገነዝበው ሁሉም ዜጎች ተዋደው፣ ተከባብረው የኖሩ ህዝቦች መኖራቸውን ነው። በመሃል ለጥቂት ጊዜ በተፈጠረው ሁኔታና ችግር ምክንያት ልዩነቶቻችንን መዘን የማውጣትና ሌሎች አመለካከቶች ሲንፀባረቁ ይታያል።

የልወቅሽ ኢትዮጵያ ንቅናቄም እነዚህን ችግሮች የመቅረፍ አላማንም በማንገብ ጭምር ነው የተነሳው። ከአንድ አካባቢ የሚነሳ ማህበረሰብ በሌላ ጥግ ያለውን የአገሩን ክፍል በሚጎበኝበት ጊዜ ባህሉም ሆነ የአኗኗር ሁኔታው ምን ያህል የተመሳሰለ እንደሆነ የማየት እድል ይኖረዋል። ምን ያህል የኢትዮጵያ ህዝብ አንዱ ጫፍ ከአንዱ ጫፍ ተመሳሳይ ነገር እንዳለው በደንብ መረዳት ይችላል።

ብዙ ነገሮቻችንን ስናይ አንድ አይነት ናቸው። በጣም የሚወደዱና የሚስቡ ባህሎች አሉን። ስለዚህ ይህ ሃብት አንዳችን በአንዳችን ማጌጥ እንድንችል ያደርገናል። ልወቅሽ ኢትዮጵያም እነዚህን አንድ የሚያደርጉንንና የሚያስተሳስሩንን ሃብቶች ልንጠቀምባቸው የምንችለው በሁሉም የአገሪቱ ክፍል ተንቀሳቅሰን መመልከትና ለማወቅ መጓጓት ስንችል እንደሆነ ያስገነዝበናል።

አስተሳሰባችን ቀና የሚሆነው ካለንበት ሰፈር ለመውጣት ፍቃደኛ ስንሆን ነው። ይህን ስናደርግ ልምድ ማግኘት እንችላለን። ይህ አካሄድ በሁሉም የዓለም ክፍል ያለና የሚሰራበት ነው። አስተሳሰባችን እንዲሰፋ መንቀሳቀስ ይኖርብናል። በዚህ ጊዜ የራሳችንን ሰጥተን የሌላውን ባህል፣ ማንነት እንዲሁም የኑሮ ብሂል መቀበልና መለዋወጥ ያስችለናል። ይህን ማድረግ የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማነቃቃት ጉልህ ሚና አለው በሚል እንደ አንድ ዋና ጉዳይ ተወስዶ ሚኒስትር መስሪያ ቤቱም ሆነ መንግስት እንደ አቅጣጫ አስቀምጦ እየሰራበት ይገኛል።

**አዲስ ዘመን፡- “ልወቅሽ ኢትዮጵያ” ንቅናቄ ምን ስምን ያህል ጊዜ ይቆያል? ተቋማዊ ቅርፅ ይዞ እንዲቀጥል፣ ዜጎች አገራቸውን የመጎብኘት ባህል እንዲኖራቸውና ዘላቂ ውጤት ለማምጣትስ ምን እየተሰራ ነው?**

**ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት፡-** የአገር ውስጥ ቱሪዝምን የማነቃቃት ግቡ በስትራቴጂ ላይ ተቀምጧል። ለረጅም አመት የሚቆይና በስፋት የሚሰራበት ነው። ይህ ዘርፍ በአገራችን እንደ ባህል ተደርጎ እስኪወሰድ ድረስ የሚቀጥል ይሆናል።

አሁን የቱሪዝም ዘርፉ ከገባበት ድብቴ እንዲላቀቅ ይህ ንቅናቄ በዋናነት ቢያስፈልግም ዜጎች ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ ስፍራ ነባርና አዳዲስ መስህቦችን ለመመልከት የሚያደርጉትን ጉዞ እንደ ባህል መውሰድ እስከሚችሉ ድረስ ይህን እንሰራበታለን።

ልወቅሽ ኢትዮጵያ ንቅናቄ እንደመሆኑ ፕሮጀክቱን ለእዚህ አመት እንጠቀምበታለን። ለቀጣይ ዓመት ደግሞ ሌላ ተመሳሳይ እና የተሻለ ሃሳብ በመፍጠርም ተከታታይ ስራዎችን እንሰራለን። “ልወቅሽ ኢትዮጵያ” ለዚህ አመት ብቻ የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ከማነቃቃት አንፃር ልንጠቀምበት ያሰብነው መሪ ሃሳብ (ሞቶ) ነው።

በውስጡም በርካታ ሁነቶች፣ ሃሳቦች፣ በተግባር ላይ የሚውሉ ድርጊቶችና ግቦችን ያነገበ ነው። በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ክልሎች የሚገኙ መስህቦች፣ የመዳረሻ ስፍራዎች እንዲሁም አዳዲስ የተሰሩ የቱሪዝም ሃብቶችን በአንድ ላይ በማካተት ተግባራዊ የሚሆን ነው።

ወጣቶች አሁን ላይ በቡድን በመሆን አዳዲስ መዳረሻዎችን የመመልከት ባህል እያዳበሩ ነው። በተለይ መልክአ ምድሮችን (ሃይኪንግ) መጎብኘት፣ በወንዞች ላይ መንሸራሸር (ራፍቲንግ) እና ሌሎች ልዩ ልዩ አዳዲስ ሃሳቦችን እየፈጠሩ የጉብኝት ባህል እንዲዳብር የሚያደርጉ ወጣቶች አሉ። ይህ ልምድ እየሆነ እየመጣ ነው። ሚኒስትር መስሪያ ቤቱም እነዚህን ወጣቶችና ቡድኖች እንደ አንድ ባለድርሻ በመውሰድ ለመስራት እየተዘጋጀ ይገኛል። የንቅናቄው አንድ አካልም ናቸው።

የቱሪዝም ሚኒስቴር መስከረምን የቱሪዝም ወር በማለት ሰይሞ ሰፊፊ ስራዎችን አከናውኗል። ለምሳሌ ያህል ለመስቀል ዜጎች ወደ ቤተሰቦቻቸው በመሄድ ባህሉን ለቀናት ቆይታ አድርገው ሲያከብሩ እግረ መንገዳቸውን በተራራ መውጣት (ሃይኪንግ) በብስክሌት ግልቢያ (ባይኪንግና) መሰል መዝናኛዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተሰርቷል። ወደ ጉራጌ ዞን ሶዶ የተደረገው ጉዞ ለእዚህ በአብነት ሊወሰድ ይቻላል። ይህንን ልምድ በየቦታው የማድረግ ሰፊ እቅድ አለ። አጋጣሚውም ዜጎች የኢትዮጵያን መልክአ ምድር በሚገባ እንዲያውቁት ከማድረጉም ባሻገር ባህልና የአኗኗር ዘይቤ እንዲገነዘቡ ያስችላል።

**አዲስ ዘመን፡- የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ከማስፋፋት አንፃር በርካታ ክፍተቶች እንደነበሩ ይታወቃል።ስለመሆኑ እነዚህ ክፍተቶች ምንድናቸው? የተቀመጠ የመፍትሄ ሃሳብስ አለን?**

**ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት፡-** የቱሪዝም ዘርፍ በተለይ የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ከማስፋፋት አንፃር በርካታ ክፍተቶች ነበሩ። ለዚህ ምክንያቱ በልዩ ልዩ የአገሪቱ የመዳረሻ ስፍራዎች ላይ የሚገኙ መስህቦች ለጎብኚዎች ምቹና የለሙ አለመሆናቸው ነው። ይህ እንደ ትልቅ ክፍተት ሊወሰድ የሚችል ነበር።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ በርካታ መስህቦችና መዳረሻዎችን በቅጡ አለማወቅም ሌላኛው ችግር ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ የሚያሳየው ሰፊ የፕሮሞሽን ወይም የማስተዋወቅ ክፍተት እንደነበር ነው። እነዚህን አንኳር አንኳር የምንላቸውን ችግሮች ለይተን መፍትሄ ለመስጠት እየሰራን ነው። በተለይ ተወዳዳሪ የሚሆን የሰው ሃይል ችግር አለ። እሱን ለማሟላት እንሰራለን። ነቅሰን ያወጣናቸው ችግሮች በቶሎ መፍትሄ እንዲያገኙም እቅድ በመንደፍ ወደ ተግባር እየገባን ነው። እስካሁን ድረስም ጥሩ ውጤት እያመጣን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለቃለ ምልልሱ ፍቃደኛ ሆነው ጊዜዎትን ስለሰጡን እናመሰግናለን!!**

**ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት፡-** እኔም አመሰግናለሁ!!

# ሳምንቱን በታሪክ

# ጥቅምት 24 እና የሰሜን ዕዝ

**ዋስልኝ አየለ**

ዕለተ ማክሰኞ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ሌሊት በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ አንድ ያልተጠበቀ ክስተት ተሰማ። የማህበራዊ ገጾች በዚህ መረጃ ተጥለቀለቁ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአገሪቱ ብሔራዊ የቴሌቭዥን ጣቢያ ብቅ ብለው መርዶውን ተናገሩ።

ሕዝቡም ከሌሊት የቀጠለ አግራሞቱን ይዞ ጠዋት «አሁንስ ምን ይፈጠር ይሆን?» እያለ የማለዳ ዜና ለመስማት አይኑን ቴሌቭዥን ላይ ተከለ። አንዳንዱ ደግሞ «አገር አማን» ብሎ ተኝቶ አድሮ ጠዋት ጥቅምት 25 ቀን አዲስ አስደንጋጭ ዜና የሰማበት ዕለት ነው። የሰማውን ማመን አቅቶት ከጎኑ ያለውን ሰው የጠየቀበት ዕለት ነው። ብዙ ሰዎች ግን ዘመኑ ባመቻቸው የማህበራዊ ድረ ገጾች አማካኝነት ክስተቱን ሌሊት ሰምተዋል።

ጥቅምት 24 ሌሊት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰጡትን መግለጫ ብዙ ሰው ሰምቷል። የዚያን ቀን ሌሊት የማህበራዊ ገጾች፣ ቀን ከሚታየው በላይ እንቅስቃሴያቸው ጨመረ። ሌሊት የሰማው ሰምቶ ያልሰማውም ተኝቶ ነጋና ጥቅምት 25 ቀን ጠዋት ግን የሁሉም ቀልብ ወደ ሰሜኑ የአገራችን ክፍል ሆነ። «ምን ይፈጠር ይሆን?» በሚል ስጋት ብዙዎች በያሉበት መጨነቅ ጀመሩ። የሁሉም ዓይንና ጆሮ የመገናኛ ብዙኃን ላይ ሆነ። ለመሆኑ በዚህ ቀን ምን ተባለ? ምን ተከሰተ?

ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ሕወሓት በሰሜን ዕዝ ላይ የፈጸመው ጥቃት የተሰማበት የመጀመሪያው ቀን ነው። ስለዝርዝር ሁኔታው ብዙ ሰው አያውቅም። ዝርዝር ጉዳዮች የተሰሙት ከቀናት በኋላ ነው። እየቆየ ግን አሳዛኝ የወንጀል አፈጻጸም ድርጊቶችም መሰማት ጀመሩ። የተለያዩ አካባቢዎች ነዋሪዎችም ቀኑን ሙሉ ድርጊቱን አወገዙ።

የሰሜን ዕዝ መጠቃት ዜና ከተሰማበት ዕለት ጀምሮ፤ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ የጦር መኮንኖች፣ ታዋቂ ሰዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የተለያዩ አካባቢዎች ነዋሪዎች፣ የተለያዩ ዘርፎች ባለሙያዎች እና በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎች ለመገናኛ ብዙኃን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ብልጽግና ፓርቲ በዕለቱ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚከተለውን መግለጫ ሰጠ።

«...ከሀገራዊ ለውጡ በፊት እንደ ሀገር መቀጠል የማንችልበት ደረጃ ላይ ስለመድረሳችን ብዙ ምክንያቶችን ማንሳት እንችላለን።

ህዝብን በጸረ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ለመምራት የሚደረግ አይን ያወጣ ተጽዕኖ፣ አድርግ ወይም አታድርግ በሚሉ ቃሎች ብቻ የተገደበ እና ህዝብን ለማሸማቀቅ በርካታ ድርጊቶች ሲፈፀሙ እንደነበር ይታወቃል።

> **ህዝብን በጸረ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ለመምራት የሚደረግ አይን ያወጣ ተጽዕኖ፣ አድርግ ወይም አታድርግ በሚሉ ቃሎች ብቻ የተገደበ እና ህዝብን ለማሸማቀቅ በርካታ ድርጊቶች ሲፈፀሙ እንደነበር ይታወቃል**

ህዝብን ከፋፍሎ የመግዛት አባዜ የተጸናወተው ጥቂት የሕወሓት ቡድኖች በርካቶች ተገፍተው ከሀገር እንዲወጡም ምክንያት ነበሩ።

ለሀገራቸው ፖለቲካ ያገባናል ያሉ የፖለቲካ ሀይሎች ሀሳባቸውን አውጥተው መግለጽ እንዳይችሉ ሲደረግባቸው የነበረውን አፈና፣ እስር፣ ግርፋት እና አሰቃቂ ድርጊቶች ለፖለቲካ ምህዳሩ መጥበብ እንደምክንያት የሚጠቀሱ ናቸው።

የመሰረተ ልማት እጥረት ባልተቀረፈበት እና የህዝብ የልማት ጥያቄዎችን መፍታት አዳጋች በሆነባት ሀገር እነዚሁ ቡድኖች በርካታ የህዝብና የመንግስት ተቋማትን በመዝረፍና የዘረፉትን ወደ ውጭ ሀገራት በማሸሽ በህዝብ ላይ ክህደት በሀገር ላይ የኢኮኖሚ ውድቀት አስከትለዋል።

እወክለዋለሁ ላለው የትግራይ ህዝብ በተጨባጭ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት የተሳነው ይህ ቡድን ከሀገራዊ ለውጡ እኩል መራመድ ባለመቻሉና ሲፈፅማቸው የነበሩ ኢ-ዴሞክራሲያዊ አካሄዶች ከህዝብ ፊት መቆም እንዳይችል ስላደረገው ውህደቱን ከመቀላቀል ይልቅ መግፋትን አማራጩ አድርጓል።

ለህገ መንግስታዊ ስርዓት ጠበቃ ነኝ ሲል የነበረው የሕወሓት ቡድን የትግራይን ህዝብ ከሌሎች ወንድም ህዝቦች ጋር ለመነጣጠልና ለህገ መንግስቱ ያለውን ንቀት ያረጋገጠበትን ህገ ወጥ ክልላዊ ምርጫ ሲያደርግና ህጋዊ ያልሆነ መንግስት ሲመሰርት በሆደ ሰፊነት የተመለከተው የፌደራል መንግስት ይህ ቡድን እየተከተለው ያለው ኢ-ህገ መንግስታዊ አካሄድ ከዛሬ ነገ ሊለወጥ ይችላል በሚል ጊዜ ሰጥቶ ቆይቷል።

ዳሩ አምባገነናዊ ባህሪው እያደገ ቢመጣም። የትግራይ ህዝብ ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ ለሀገራዊ ለውጡ በጋራ ለመቆም ፍላጎት ቢኖረውም ጥቂት የሕወሓት ቡድን አመራሮች ግን የህዝቡን ፍላጎት ወደ ጎን በመግፋት ህዝቡ ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንዳይኖረው ጭቆና ሲያደርስበት ቆይቷል።

ብልጽግናና የለውጡ መሪዎች ሕወሓት ውህደቱን እንዲፈጽምና ለጋራ ሀገራችን በጋራ እንቁም መርህ በተደጋጋሚ ጊዜ የድርጅቱን መሪዎች በማግኘት ሰፊ ጊዜ ተወስዶ ማወያየት ቢቻልም ወትሮውንም ሀገርንና ህዝብን የማገልገል ጽኑ ፍላጎት ሳይሆን ጥያቄያቸው በስልጣን የሚገኝ ጥቅምን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ለውህደቱ እምቢታቸውን አሳይተዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ተስፋ ያልቆረጡት የለውጡ መሪዎች በህዝብ የሚታወቁም ሆነ የማይታወቁ በርካታ ጥረቶችን በማድረግ የትግራይን ህዝብ ከለውጡ ጋር አብሮ ለማስቀጠል ያላሰለሰ ግፊት ቢደረግም በጸረ ለውጥ ቡድኖች ሰንኮፍነት እንደታሰበው ውህደቱን ለማቀላቀል የተደረገው ጥረት ያለ ውጤት ተጠናቋል።

መቀሌ የመሸገው ቡድኑ ምስኪኑን የትግራይ ህዝብ ጠዋት ማታ የአማራ ክልልና የፌደራል መንግስት ጦርነት በህዝባችን ላይ ሊከፍቱብን ነው በሚል የተሳሳተ መረጃ ህዝቡን በማደናገር እረፍት አሳጥቶት ከርሟል።

የትግራይ ህዝብ ጦርነት እንዳንገሸገሸው የኢትዮጵያ ህዝብ ከልብ ይረዳዋል።

ጦርነት የመጨረሻ እንጂ የመጀመሪያ አማራጭ እንዳልሆነ ብልጽግና ይገነዘባል።

የመከላከያ ሰራዊቱን ከክልሉ ፈቃድ ውጭ ማደራጀት አትችሉም የሚል አቋም እየተከተለ ያለው ሴረኛውና ጥቂቱ የሕወሓት ቡድን የፌደራል መንግስትን ውሳኔዎችና የሚሰጡ አቅጣጫዎችን ተግባራዊ እንዳይሆኑ ግትር አቋሙን ሲያሳይ ቆይቷል።

ከህዝብ አብራክ ወጥቶ ህዝብንና ሀገርን ከጥቃት እየተከላከለ የሚገኘውን የመከላከያ ሰራዊቱን የቆየ ክብርና ዝና ለማጠልሸት ሲሞክር ሆደ ሰፊው ሰራዊት ምላሽ ሳይሰጥ ቆይቷል።

ይሁን እንጂ ለጥፋት ሁሌም የማይተኛው ጥቂት የሕወሓት ቡድን አማካኝነት በተሰጠው ትዕዛዝ በትግራይ በሚገኘው የመከላከያ ካምፕና ከሃያ ዓመታት በላይ የትግራይን ሕዝብ ሲጠብቅ የቆየ ሠራዊት ላይ ሌሊት በተኛበት ጥቃት ከማድረሳቸው ባሻገር ሰሜን ዕዝንም ለመዝረፍ ሙከራ አድርገዋል።

ነገሩን በሆደ ሰፊነት ሲመለከተው የቆየው መንግስት እየተፈፀሙ ያሉ ድርጊቶች ገደብ በማለፋቸውና ግልጽ ትንኮሳ በመፈጠሩ ምክንያት ይህንኑ ድርጊት ሊመክት የሚችል አጸፋዊ እርምጃ ለመውሰድ ተገዷል።

በዚህ መሀል ምንም የማያውቀው የትግራይ ህዝብ ተጎጂ እንዳይሆን አስፈላጊውን ጥንቃቄ እየተወሰደ ይገኛል።

በአጠቃላይ ከዚህ በፊት እንደምናደርገው ሁሉ ብልጽግና ፓርቲ ለሀገርና ለህዝብ ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ሌት ተቀን የሚሰራና የህዝብንና ሀገርን ሰላም አደጋ ውስጥ ሊከት የሚችል ማናቸውንም ነገሮች ለመታገስ እንደማይችል ታውቆ በተሣሣተ መረጃ ጭቁኑን የትግራይ ህዝብ ላይ ያልተገባ ስጋት በመፍጠር ተጠራጣሪ ለማድረግ የሚደረገው ተከታታይ ቅስቀሳ የትግራይ ህዝብ ሊያወግዘው የሚገባ መሆኑን በፅኑ በማመን የሚከተሉትን የአብሮነትና የአጋርነት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

**1. ለተከበርከው የትግራይ ህዝብ**

የትግራይ ህዝብ ከሌሎቹ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጋር ጠንካራ ታሪካዊ አንድነትና ውህደት ያላቸው፣ ባህላዊና ጥንታዊ ሃይማኖታዊ እሴቶችን የሚጋሩ፣ በጋብቻና በደም የተሳሰሩ፣ በፀረ-ጭቆና ትግል ከሌሎች ህዝቦች ጋር ሆነው በአንድ ጉድጓድ ክቡር መስዋዕትነት እየከፈሉ አሁን ላለንበት የሀገረ መንግስት ምስረታ ጉልህ አሻራ ያሳረፉ ህዝቦች ናቸው። ሆኖም የሕወሓት ቡድን የሀገርንና የህዝብን ሰላምና ደህንነት አደጋ ላይ ለመጣል የሚያደርጉት ሴራ መሆኑን አውቃችሁ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ያላችሁ ወንድማዊና ቤተሰባዊ ግንኙነታችሁ ሳይቋረጥ የትግራይን ህዝብ የሚያለያዩ ሙከራዎችን በፅናት እንድትታገሉ የከበረ ጥሪያችንን እያቀረብን በዚህ ቡድን ላይ እርምጃ በመውሰድ ህብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ለማስቀጠል በምናደርገው ትግል ውስጥ ከጎናችን እንድትሆኑ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**2. ለመላው የትግራይ ምሁራን**

ሀገርን በሚፈለገው ደረጃ መለወጥ ካስፈለገ ምሁራን የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ከፍ ያለውን ቦታ መያዙ ግልጽ ነው።

ሆኖም ግን ሕወሓት በክልሉ የሚገኙ ምሁራንን ለሀገራቸው ሁለንተናዊ አበርክቶ እንዳያደርጉ በጥቅም የተሳሰረው ቡድን እንቅፋት እንደሆነባችሁ መረዳት ተችሏል።

ስለሆነም ምሁራን በነጻነት ተንቀሳቅሰው ያላቸውን አቅምና ዕውቀት ለሀገራችን ህዝቦች እንዲያበረክቱ ካስፈለገ ጨቋኙንና ጸረ ለውጡን የሕወሓት ቡድን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማስወገድ ያስፈልጋል።

ስለሆነም የተከበራችሁ በትግራይ የምትገኙ ምሁራን ሁላችሁም የፌደራል መንግስት በክልሉ እያደረገ ያለው ህገ መንግስቱን ማስከበር ስራ በውጤታማነት ለመፈፀም እንዲቻል የበኩላችሁን ሚና እንድትወጡ የአክብሮት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

**3. ለመላው የትግራይ ወጣቶች**

በክልሉ የምትገኙ ወጣቶች ምንም አይነት ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ መሆን ሳትችሉ ነገር ግን በስማችሁ እየተነገደ ለበርካታ ዓመታት ቆይታችኋል።

ይህንን አይን ያወጣ ዘረፋና ሌብነት በሕወሓት ቡድን አማካኝነት ሲካሄድ እንደነበርም የአደባባይ ሀቅ ነው።

በስሙ ሲነገድበት ለቆየው የትግራይ ወጣት ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ይረጋገጥ ዘንድ በዚህ ቡድን ላይ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷልና መላው የትግራይ ወጣቶች በፌደራል መንግስት በኩል እየተወሰደ ያለውን ህግን የማስከበር እርምጃ በመደገፍ ለክልሉና ለሀገር ሰላም አጋር እንድትሆኑ የትግራይ ወጣቶች ከመላው የሀገራችን ወጣቶች ጋር በመሆን የጀመርነውን አገራዊ ለውጥ አጠናክረን እንድንቀጥል ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**4. በትግራይ ክልል ለምትገኙ የክልሉ የፀጥታ ሃይሎች**

የትግራይ ክልል የፀጥታ ሀይሎች በሀገሪቱ ከሚገኙ የፀጥታ ሃይሎች ጋር በጋራ በመሆን ህዝባዊነታችሁን ጠብቃችሁ ለአንዲት ሉአላዊት አገር መከበርና ቀጣይነት ክቡር መስዋዕትነት በመክፈል ላይ መሆናችሁን ብልጽግና ፓርቲ ከልብ ይገነዘባል።

ምንም እንኳ በክልሉ አምባገነን የሆነው የሕወሓት ቡድን በትግራይ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን እንግልትና ስቃይ የታዘባችሁ ቢሆንም ባለው ጸረ-ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ምክንያት ለውጡን ከህዝባችሁ ጋር ሆናችሁ ማጣጣም ሳትችሉ ቀርታችኋል።

ሆኖም ለረዥም ዓመታት የክልሉን ህዝብ ሰላም ደህንነት በሀላፊነት መንፈስ ወስዳችሁ ስትጠብቁ የቆያችሁ የክልሉ ፖሊስ፣ ልዩ ሀይል አባላትና ሌሎችም በህዝብ ትከሻ ላይ ሆኖ እየቀለደ ባለው ዘራፊና አጥፊ የሕወሓት ቡድን ላይ እርምጃ ለመውሰድ እየተደረገ ያለውን ትግል በመቀላቀል ህዝባዊነታችሁን እንድታረጋግጡ በድጋሚ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ

ጥቅምት 25 ቀን 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ...»

ጥቅምት 26 ቀን 2013 ዓ.ም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 6ኛ ዓመት 3ኛ መደበኛ ጉባኤውን አካሄደ። ከምክር ቤቱ የዕለቱ አጀንዳዎች መካከልም፤ ህገ መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርአቱን ከአደጋ ለመከላከል በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ለማፅደቅ እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ አባላትን ለመሰየም የሚቀርብለትን የውሳኔ ሀሳብም ለማጽደቅ ነው። የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መርምሮ በስድስት ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል። ጠቅላይ ዓቃቤ ህግም በዕለቱ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ላይ ማብራሪያ ሰጥቷል።

እንዲህ እንዲህ እያለ ሳምንቱ በሙሉ የመግለጫዎችና የውግዘት ዜና ሆኖ ሰነበተ። እነሆ የዚያን ጊዜ የተጀመረው ጦርነት ጦሱ ለሁለት ዓመታት ያህል ቀጥሎ፤ ልክ በሁለተኛ ዓመቱ ዋዜማ ግን ሌላ አስደሳች ዜና ተሰማ። የፌዴራሉ መንግሥትና ሕወሓት በደቡብ አፍሪካ ለ10 ቀናት ያህል ያደረጉት የሰላም ድርድር ተጠናቆ ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም መግለጫ ተሰጠ። ይህም የታሪክ አካል ሆኖ ይቀመጣል። በአኩሪ ታሪኮቻችን እንኩራ፤ ከስህተቶቻችን እንማር!

የመከላከያ ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ኮሎኔል ጌትነት አዳነ ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጡት መግለጫ፤ ጥቅምት 24 የሚታወሰው የአሸናፊና ተሸናፊ ትርክት ለመፍጠር ሳይሆን ተመሳሳይ ታሪክ እንዳይደገም ነው።

# የዝነኞች ገጽ

## ሙናዬ መንበሩ

**አቤል ገብረኪዳን**

ተወልዳ ያደገችው እዚሁ አዲስ አበባ ቀጨኔ አካባቢ ነው። ወቅቱም ነሐሴ 10 ቀን 1939 ዓ.ም ነበር። የአንጋፋው ሀገር ፍቅር ቴአትር የመድረክ ፈርጦች መካከልም አንዷ ነበረች፤ ሙናዬ መንበሩ። እጅጉን ዕውቅናን የገበየችበት በተዋናይነቷ ቢሆንም ተወዳጅ ሙዚቀኛም ነበረች። በተለይ "ጉብልዬ"፣ "ብርቱካኔ" እና "ትዝታዬ" የተሰኙት ሙዚቃዎቿ ደግሞ ታዋቂ ነበሩ። ዘወትር ዓርብ ምሽት በኢትዮጵያ ሬዲዮ ይተላለፍ የነበረውን "የባህል ሙዚቃ ዝግጅት" ይከታተል የነበረ ሰው አይስታቸውም።

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ጥበቡ ዓለም የዘለቀችው በ1952 ዓ.ም ነበር። የሰፈሯ ነዋሪ የነበሩት ታዋቂው የጥበብ ሰውና ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ አገር የተዳረበትን "ሙሽራዬ" የተባለውን ሙዚቃ የደረሱት አቶ በሻህ ተክለማርያም ነበሩ ከጓደኞቿ ጋር ለእንቁጣጣሽ ቤታቸው መጥታ ስትጨፍር አይተዋት ይሰሩበት ከነበረው ሀገር ፍቅር ቴአትር ወስደው ያስቀጠሯት። እሷም በወቅቱ ደሃ ቤተሰቦቿን የመርዳት ጉጉት ስለነበራት በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት ትከታተለው የነበረውን ትምህርቷን ከ3ኛ ክፍል በማቋረጥ በወር 15 ብር ክፍያ እየተከፈላት ለመስራት ዓይኗን አላሸችም ነበር። በሁለገብ ባለሙያነቷ የምትታወቀው ሙናዬ መንበሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ተዋናይነትን የጀመረችው "ምቀኛው ዕድሌ አደረገኝ ሎሌ" በተሰኘው የአርቲስት ቀለመወርቅ ደበበ ድርሰት ነበር። ከዚያ በኋላ በህዝብ ዘንድ እጅግ ታዋቂ ትሆን ዘንድ ያስቻላትን "የቀለጠው መንደር" ቴአትርን ጨምሮ ከመቶ በላይ ተውኔቶች ላይ ለመተወን በቅታለች። ሙናዬን ሳስባት ቀድሞ ከፊቴ ድቅን የሚልብኝ በዚህ ቴአትር ላይ ታደርገው የነበረው እንቅስቃሴ፣ ንግግሯና አጠቃላይ ችሎታዋም ነው።

በሙያዊ ስነ-ምግባሯና ለጥበብ ታዳሚያን በነበራት አክብሮት ሁሌም የምትታወሰው ይህች አርቲስት ለዚህ መገለጫ የሚሆን ብዙ ታሪክም አላት። ሙናዬ በንጉሱ ዘመን ከአራስ ቤት ወጥታ መድረክ እየሰራች ልጇ ሞተችና ተነገራት። በአጋጣሚ የምትተውንበት ገጸ ባህሪ የሚያስለቅስ ስለነበረ እያለቀሰች ጨረሰችው። ከትያትሩ በኋላ ለታዳሚው ተነግሮት አጅቧት ሄዶ በቀብሩ ላይ ተገኘ። ንጉሱም ሰምተው የደመወዝ ጭማሪ ተደረገላት። በ1984 ዓ.ም ደግሞ የመጨረሻ ታዳጊ ልጇ በፈረንሳይ ለጋሲዮን ማዞሪያ ቤቷ አካባቢ በጥይት ተገደለባት። ያን ቀንም ከተማው እየታመሰ እሷ ግን ስራዋን ብላ ሀገር ፍቅር ተገኝታ ነበር። ልምምድ አድርጋ ወደ ቤቷ ስትመለስ ነበር ወሬውን የሰማችው። የካቲት 12 ሆስፒታል ስትደርስ ልጇን አይታው አረፈ።

ሙናዬ ከስራ ባልደረባዋ አቶ በቀለ ወልደጻዲቅ ጋር በመሰረተችው ትዳር አምስት ልጆች አፍርታለች። እነዚህን አምስት ልጆች ወልዳ ባሳደገችባቸው ዓመታት በሙሉ ሀገር ፍቅር ስትሰራ የነበረ ሲሆን፤ ከ40 ዓመታት በላይ በሰራችበት ቴአትር ቤት በ15 ብር ተቀጥራ ከአራት አስርት ዓመታት በኋላም ግን ደሞዟ ከሰባት መቶ ብር ጥቂት ነበር ከፍ የሚለው። እንዲያም ቢሆን ግን ሙያዋን ስለምትወደው ገንዘብ አነሰኝ ብላ አማርራ አታውቅም። በእርግጥ በአንድ ወቅት በወዷጇ አሰለፈች አሸኔ ድጋፍ ካዛንቺስ አካባቢ ግሮሰሪ ከፍታ የነበረ ቢሆንም ሁለት ስራ መስራት አይቻልም ተብላ ቴአትሯን መርጣ ንግዱን ትታዋለች።

ሙናዬ በስራዋ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ቻይና፣ ሩሲያ፣ ኬንያ እና ሱዳን ተጉዛለች። የፈረንሳዩ ጉዞ የራሱ ታሪክ አለው። ሙናዬ በወቅቱ ነፍሰ ጡር ነበረች፤ ይህን የሚያውቁ ሰዎችም ወደ ቴአትር ቤቱ ስራ አስኪያጅ ሄደው ሙናዬ ነፍሰ ጡር ናት መሄድ አይገባትም ብለው ከሰሷት። ቢሮ ተጠርታም ነፍሰ ጡር ነሽ ወይ ተባለች እሷ ግን አይደለሁም ብላ ካደች። ተመርምረሽ አምጪ በመባሏም ጤና ጣቢያ ሄደች። ወቅቱ ደግሞ ጉብልዬ የተባለው ዘፈኗ በጣም ተወዳጅ የሆነበት ጊዜ ነበርና ነርሷ እንዳየቻት አወቀቻት። ምን ሆና እንደመጣችም ጠየቀቻት፤ እንዲህ አይነት ነገር አጋጥሞኝ ነው ስትላት ነርሷ ለሀኪሙ ጉዳዩን ነገረችው። ሙናዬም ነፍሰ ጡር አይደለችም ተባለ። አለቃዋ ይሄን ሲሰሙ በቃ ትሂድ በማለታቸው ፈረንሳይ ሄዳ ስራዋን በአግባቡ ተወጥታ ተመለሰች።

ደግሞ ሌላም ገጠመኝ አላት፤ ወቅቱ 1950 ዓ.ም ነው። "የእድሜ ልክ እስራት" ቴአትር ጅማዎችን አስደምሟል። የማቲያስ በቀለ ድርሰት ነው። ከሃገር ፍቅር ማኅበር ተዋናዮች ደግሞ ሙናዬ መንበሩ ድንቅ ተብላለች። እናም ተወዳጁ ቴአትር ይደገም ተብሎ ቀጠሮ ተይዞለታል። ሆኖም ይታያል በተባለበት ቀን ሙናዬ ታመመች። ለመስራት ብታስብም ህመሙ ካቅሟ በላይ ሆነ። ደግነቱ የሙናዬን ገጸ ባህሪ ያጠናች ባለሙያ አለችና እነሱ ትርዒቱን ሊያቀርቡ ሄዱ። ሙናዬስ ትሉ ይሆናል? እሷማ ከህመሟ ጋ እየታገለች ያላለቀ አንድ የጭቃ ቤት ውስጥ ጋደም ብላለች። ያኔ አቅሙ ስላልነበራቸው ሆቴል መያዝ አይችሉም። የውሎ አበል እንኳን የለም። ወይ መኪናቸው ውስጥ ያድራሉ አለበለዛም ጅምር ቤት ካገኙ ባለቤቱን አስፈቅደው ለጥ ይላሉ። ሙናዬም በእንደዚህ በተገኘ ታዛ ውስጥ ነበር ህመሟን እያማጠች ያለችው። ግና ከህመሟ በላይ በጭካኔ ነፍስን የሚያወጣ አውሬ ከበባት፤ የጅብ መንጋ። እዚህ ላይ ቀልድ የለም። ነፍሷን ለማትረፍ የድረሱልኝ ኡኡታ አሰማች። ተመስገን፤ ፈጥኖ ደራሽ ጎረቤት አይጥፋ። የተንጋጋውን ጅብ ተንጋግተው መጡና ከመበላት አተረፏት።

የሙናዬ የልብ ጓደኛ በላይነሽ አመዴ ናት፤ የሁለቱ ፍቅር ይለይ ነበር። ሙናዬ ጓደኛዋን ስታቆላምጣት በላይነሽ አመዴ ልቅም እንደስንዴ ይወድሻል ሆዴ ትላታለች። አብረው ሰርተዋል፤ አብረውም ኖረዋል። ሙናዬ በትወናዋ ላይ የሚሰጣት ገጸ ባህሪ ብዙውን ጊዜ የኃይለኛ ሴት ቢሆንም በመደበኛ ባህሪዋ ግን ሳቂታ እና ጨዋታ ወዳድ ናት። መዝናናትን እንደምትወድ የምትናገረው ሙናዬ ጭቅጭቅ እና ኩርፊያን እንደምትጠላም ተናግራለች። የአምስት ልጆቿን አባት ከማግባቷ በፊት የነበረውን ባለቤቷን የፈታችውም በአኩራፊነቱ እና ቀናተኝነቱ እንደሆነ ትናገራለች። አብረዋት የሰሩትም ሰዎች ሙናዬ ቂም የማታውቅ አገር ሰው ናት ይሏታል። ይህች የመድረክ ፈርጥ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየችው ነሐሴ 10 ቀን 1995 ዓ.ም ነበር።


ተዋናይትና ድምጻዊ ሙናዬ መንበሩ፤

## መልካሙ ተበጀ


ድምጻዊ መልካሙ ተበጀ፤

በዚህ ዘመን ሙዚቃቸው እንደ አዲስ እየተደመ ጠላቸው ካሉ አንጋፋ ድምጻውያን መካከል አንዱ አንጋፋው አርቲስት መልካሙ ተበጀ ነው። በየትኛውም የምሽት ክበብ ቢገባ የመልካሙን ሙዚቃ አንድ ወጣት ድምጻዊ ሲጫወተው መስማት የተለመደ ነው። ሚክስ እየተደረጉ እንደ አዲስ ከተዘፈኑ ሙዚቃዎች ውስጥም የመልካሙን ሙዚቃ በተደጋጋሚ መስማት የተለመደ ነው። የፊልም ማጀቢያ ሆነው በድጋሚ የተዘፈኑ ሙዚቃዎችም አሉት።

መልካሙ ተበጀ የተወለደው በ1938 ዓ.ም በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ክብረ መንግስት በሚባል ቦታ ነው። መልካሙ የሙዚቃ ፍቅር ከህጻንነቱ ጀምሮ አብሮት ያደገ ነው። ቤተሰቦቹ ለስራ ጉዳይ ወደ ሃረር ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ሲዘዋወሩ አብሮ በመምጣት በአምሃ ደስታ ትምህርት ቤት ይገባል። በትምህርት ቤት የተለያዩ በዓላት በተለይም በወላጆች ቀን በሚያደርገው ተሳትፎ የሙዚቃ ስሜቱ ከእሱ አልፎ በተመልካች ዘንድ እየጎላ በመሄድ ነሐሴ 15 ቀን 1957 ዓ.ም በብሄራዊ ቲአትር የታዳጊ ኦርኬስትራ (ዳዊት ኦርኬስትራ) በድምጻዊነት ተቀጠረ። ከዚያን በኋላ በርካታ ስራዎችን የተጫወተ ሲሆን ራሱ ከመዝፈኑ ባለፈ ለብዙ ድምጻውያንም ዜማ እና ግጥምም ሰጥቷል።

ራሱ መልካሙ ከተጫወታቸው ዜማዎች መካከልም አብዛኞቹ የራሱ ድርሰቶች ናቸው። ከነዚህም መካከል «የሲዳሞ ቆንጆ»፣ «በይ እንግዲህ ተለያየን»፣ «ቸብ ቸብ»፣ «ዳህላክ» እና «ሙዚቃ» የተሰኙ ዜማዎቹ እራሱ ደርሶ ከተጫወታቸው ዘፈኖች መካከል በዋቢነት ሊዘከሩ የሚችሉ ናቸው። የሲዳሞ ወጣት ራሱ መልካሙ የትውልድ ስፍራው ሲዳሞ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ስለ ትውልድ ስፍራው ወጣት ሴት የተጫወተው ነው። ቸብ ቸብ አርጉላት አሁን ላይ ዋነኛ የሰርግ ማድመቂያ ሙዚቃ ሆኖለታል። ልቤ አይስቅልሽም እና ባር ባር ሲለው ሆዱ በቀድሞው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ስቱዲዮ ተቀርጸው ለብዙ ዓመታት የህብረት ትርኢት የሙዚቃ ፕሮግራም ላይ ህዝብ ያያቸው እና የወደዳቸውም ናቸው። ኧረ መላ ምቱ ብዙ ፍቅረኞች ታሪክ ውስጥ ያለ ተወዳጅ ሙዚቃ ነው። መልካሙ ለብቻው ከተጫወታቸው ሙዚቃዎች በተጨማሪ ከሂሩት በቀለ ጋር የተጫወተው ሙዚቃም አለው።

መልካሙ ከድምጻዊነቱ ብሎም ከግጥምና ዜማ ደራሲነቱ ባሻገር ቲአትርም የመድረስና በተዋናይነት የመሳተፍ ችሎታ ያለው አንጋፋ ከያኒ ነው። የድርሰት ችሎታውን ካስመሰከረባቸው ስራዎቹ አንዱ የሆነውና እራሱም በተዋናይነት የተሳተፈበት «ቢሮክራሲያዊ የከበርቴ አሻጥር» የተሰኘው ድርሰቱ አንዱ ነው። መልካሙ በበርካታ የቴሌቪዥን ድራማዎች ከመጫወቱ ሌላ በጸጋዬ ገብረመድህን በተደረሰው «አቡጊዳ ቀይሶ» በአያልነህ ሙላት በተደረሰው «ሻጥር በየፈርጁ» እና በሌሎችም ቴአትሮች ተሳትፏል። መልካሙ ተበጀ ስለ ማህበራዊ ሕይወት፣ ስለወጣነት ስለ ተፈጥሮ ስለፍቅር እና ስለ ሌሎችም ብዙ የተጫወተ መልከ መልካም አንጋፋ ከያኒ ነው።

ተወዳጁና አይረሴው አርቲስት መልካሙ ተበጀ በዚህ ወቅት በአሜሪካ ዲሲ ይኖራል።

ከመልካሙ እውቅ ሥራዎች መካከል...

* ነኝ ወይ ላንቺ ከፋ
* አመሰግናለሁ
* ደህና ሁኚ
* ያን ጎራ ያን ሰፈር
* የልቤን አዳራሽ
* ቸብ ቸብ አርጉላት
* ልቤ አይስቅልሽም
* የስብራቴ
* የናፍቆት ሰላምታ
* ባለማተቢቱ
* አንድ ዓመት ወደድኳት ጥቂቶቹ ሲሆኑ

በራሱ ግጥምና ዜማ የተሠሩት ሙዚቃዎቹ

* የሲዳሞ ቆንጆ
* ስንቱን አሳለፍነው
* አልጓጓም
* እንታረቅ
* ሂሩትዬ
* እንቆቅልሽ ኑሮ
* የድህነት ሚስቴ
* አንቺ ተማሪ
* አትፍረዱብኝ.....

እነዚህ ግጥምም ዜማም በመልካሙ ተበጀ የተደረሱ ሲሆን "በእንባ ተለያየን" የሚለው ተወዳጅ ሙዚቃው ዜማው የወንድሙ ቶላ ሲሆን ግጥሙ የራሱ የመልካሙ ተበጀ ነው።

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ ለድሃ የአፍሪካ ሀገራት ስንዴ በነጻ ልትሰጥ ነው

ሩሲያ ለድሃ የአፍሪካ ሀገራት ከምትልከው የስንዴ ምርት ተጠቃሚ ከሚሆኑ አገራት መካካል ሶማሊያ፣ ጅቡቲ እና ሱዳን እንደሚገኙበት ተገልጿል።

የሩሲያ ዩክሬን ጦርነት ከተጀመረ ስምንት ወራት ያለፈው ሲሆን በየጊዜው አዳዲስ ክስተቶችን በማስተናገድ ላይ ይገኛል። በዚህ ጦርነት ምክንያት የዓለም ምግብ እና ነዳጅ ዋጋ መናርን ያመጣ ሲሆን፤ ምግብ እና ነዳጅ ከውጭ ሀገራት የሚያስገቡ ሀገራትን ደግሞ የበለጠ ለአደጋ አጋልጧል።

የዩክሬን እና ሩሲያ የውጭ ንግድ ዋነኛ መስመር የሆነው ጥቁር ባህር በጦርነቱ ምክንያት አገልግሎት አቋርጦ የነበረ ሲሆን በተመድ እና ቱርክ አሸማጋይነት ይህ የንግድ መስመር ወደ አገልግሎት ተመልሷል። ሮይተርስ እንደዘገበው ከሆነ የቱርክ ፕሬዝዳንት ረሲፕ ኤርዶሃን ከሩሲያ አቻቸው ቭለድሚር ፑቲን ጋር በስልክ ባደረጉት ውይይት ሩሲያ በነጻ ስንዴዋን ወደ ድሃ ሀገራት ለማጓጓዝ መስማማቷ ተገልጿል።

የሩሲያን ስንዴ በነጻ ከሚሰጣቸው ሀገራት መካከልም ሶማሊያ፣ ጅቡቲ እና ሱዳን የተጠቀሱ ሲሆን ሀገራቱ የምግብ ችግር እንዳለባቸውም በዘገባው ላይ ተጠቅሷል። በተመድ እና ቱርክ አደራዳሪነት በጥቁር ባህር የጉዞ እና የንግድ መስመር ላይ ከ10 ሚሊዮን በላይ ቶን ስንዴ መጓጓዙ ተገልጿል።

ዩክሬን በፈረንጆቹ 2014 ላይ በህዝበ ውሳኔ ወደ ሩሲያ በተቀላቀለችው ክሪሚያ ላይ የድሮን ጥቃት አድርሳለች በሚል ሩሲያ ከጥቁር ባህር ትራንስፖርት ስምምነት መውጣቷን ተናግራ ነበር። ይሁንና ዳግም በተደረገ ድርድር ዩክሬን በጥቁር ባህር ላይ ጥቃት እንደማትከፍት የጽሁፍ ማረጋገጫ መስጠቷን ተከትሎ ሩሲያ ወደ ስምምነቱ ዳግም መመለሷን ማስታወቋን አልዐይን ዘግቧል።

የሩሲያ ፕሬዝዳንት ቭላድሚር ፑቲን ከዚህ በፊት ሞስኮ የአፈር ማዳበሪያ ምርቶቿን ለአፍሪካ ሀገራት በነጻ እንደምታጓጉዝ መናገራቸው ይታወሳል።

## የፈረንሳይ የፓርላማ አባል “በዘረኛ” ንግግራቸው ከሥራ ታገዱ



የፈረንሳይ ቀኝ አክራሪ ፓርቲ የፓርላማ አባል ጥቁር ባልደረባቸው ስለስደተኞች እየተናገሩ ባለበት ሰዓት “ወደ አፍሪካ ሊመለሱ ይገባል!” በማለት ምክር ቤቱ ውስጥ በመጮሃቸው ከሥራቸው ለ15 ቀናት ታገዱ። የፓርላማ አባሉ ግሪጎሪ ዲ ፎርናስ፣ ንግግራቸው ባልደረባቸውን ካርሎስ ማርቲንስ ቢሎንጎን ኢላማ ያደረገ እንዳልሆነ ተናግረዋል።

“ንግግሬ በባሕር አቋርጠው ወደ አውሮፓ ለመግባት የሚሞክሩ ስደተኞችን የተመለከተ ነው” ብለዋል ፎርናስ። ፈረንሳይ ውስጥ የተወለዱት ጥቁሩ የፓርላማ አባል ቢሎንጎ ግን የባልደረባቸውን ንግግር “አሳፋሪ” ሲሉ ገልጸውታል። ይህንን ተከትሎ ዓርብ ዕለት የፓርላማ አባላት እርሳቸውን ከምክር ቤቱ ለማገድ እና ገቢያቸውን ለመቀነስ ድምጽ ሰጥተዋል። በዚህም የፓርላማ አባሉ ለ15 ቀናት ከምክር ቤቱ የታገዱ ሲሆን፣ ውሳኔው በምክር ቤቱ የተሰጠ “እጅግ ከባዱ እቀባ” እንደሆነ ተገልጿል።

ቢሎንጎ፣ በቅርብ ቀናት የባሕር ሲሳይ ከመሆን ለተረፉት 234 ስደተኞች ማረፊያ ለመፈለግ ኤስኦኤስ ሜዲትራኒያን የተሰኘ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ያቀረበውን የእርዳታ ጥያቄ በተመለከተ ለፈረንሳይ መንግሥት ጥያቄ እያቀረቡ ባለበት ወቅት ነበር ፎርናስ አስተያየቱን የሰጡት።

የናሽናል ራሊ ፓርቲ አባሉ ስደተኞችን በተመለከተ አስተያየት የሚሰጡ ከሆነ ብዙ ቁጥርን የሚያመለክቱ ቃላትን መጠቀም ነበረባቸው በሚልም የሃሳባቸው ትክክለኛ ትርጉም አካራካሪ ሆኖ ነበር። ፎርናስ፣ ከማይክራፎን ውጭ የተቀዳውና በፈረንሳይኛ ቋንቋ የሰጡት አስተያየት “ወደ አፍሪካ ሊመለስ ይገባል” የሚል ቢሆንም፣ ነጠላ እና ብዙ ቁጥር የሚያመለክቱት ቃላት ተመሳሳይ ድምጸት ስለነበራቸው ንግግራቸው አወዛግቧል።

ይህም ንግግራቸው የምክር ቤት አባሉን የሚመለከት ነው የሚል አሻሚ ትርጉምን በመያዙ ነው፣ ንግግራቸው ቅሬታን የፈጠረው። የግራ ዘመሙ ፍራንስ አንባውድ ፓርቲ የፓርላማ አባሉ ቢሎንጎ በበኩሉ “ዛሬ በቆዳዬ ቀለም መጥቷል። የተወለድኩት ፈረንሳይ ነው። ፈረንሳያዊ የፓርላማ አባልም ነኝ” ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ኤልዛቤጥ ቦርን “ለዘረኝነት ምንም ዓይነት ቦታ የለንም” ያሉ ሲሆን፣ የውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ጀራልድ ዳርማኒን በበኩላቸው የፓርላማ አባሉ ከሥራ መልቀቅ አለባቸው ብለዋል። ፎርናስ፣ አስተያየቱን የሰጡት ስደተኞችን ወደ አውሮፓ የምታጓጉዘውን ጀልባ ቢሎንጎ እየጠቀሱ እያለ ነው ሲሉ የቀረበባቸውን ክስ አልተቀበሉትም።

የፓርቲያቸው መሪ ማሪን ሊ ፔን በበኩላቸው ተቃዋሚዎቻቸውን “ያልተገባ ጩኸት ፈጥረዋል” ሲሉ ከስሰዋል። ይሁን እንጂ በኋላ ላይ ፎርናስ የሰጡት አስተያየት ቢሎንጎን ጎድቶት ከሆነ ለተፈጠረው አለመግባባት ይቅርታ ጠይቀዋል።

የግራ ዘመሙ ኤልኤፍአይ ፓርቲ መሪ ጂን ሉክ መለንቾን በትዊተር ገጻቸው ባሰፈሩት ጽሑፍ የፓርላማ አባሉ የሰጡት አስተያየት “የምንታገሰው አይደለም” ሲሉ ከምክር ቤቱ መባረር አለባቸው ብለዋል።

በዚህ ዓመት በተካሄደውና በፓርቲው ፕሬዝዳንታዊ እና የፓርላማ የምርጫ ዘመቻዎች ስደት ዋነኛ መከራከሪያ ነጥብ የነበረ ሲሆን፣ የቀኝ አክራሪው ፓርቲ መሪዋ ሊ ፔን፣ ፕሬዚደንት ሆነው ከተመረጡ ስደተኞችን ለመቀነስ የሚያስችል ሃሳብ አቅርበው እንደነበር ቢቢሲ ዘግቧል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ግዥ አስተዳደር ዳሬክቶሬት ቢሮ በ2015 በጀት አመት በኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ ሥርዓት (Electronic Government Procurement system) በመጠቀም በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ አወዳድሮ ግዥ መፈጸም ይፈልጋል፡፡

ጨረታው የሚከናወነው በኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥና ማስወገድ ሽያጭ መመሪያ 814/2013 መሰረት በ e-GP ሲስተም የጨረታ ሰነድ አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡

በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች በኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ ሥርዓት ድረ-ገጽ www.ppa.gov.et ላይ e-GP portal የሚለውን በመጫን ጨረታውን ማግኘት የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ለበለጠ መረጃ በአጭር የስልክ ቁጥር 9430 በመደወል ስለሲስተሙ መረጃ ማግኘት የሚቻል መሆኑን እያሳወቅን የጨረታው ማብቂያ ቀን ሲስተሙ ላይ በተዘጋጀው ዝርዝር የጨረታ ማስታወቂያ መመልከት ይቻላል፡፡

**የግዥ መለያ ቁጥር**

1- Procurment of Medicine- AAU-NCB G-0001-2015/22

2- Procurment of Stationary Items- AAU-NCB G-0009-2015/22

3- Procurment of Cleaning Material- AAU-NCB G-0010-2015/22

4- Procurment of Food Oil- AAU-NCB G-0012-2015/22

5- Procurment of Employee Uniform & shoes- AAU-NCB G-0014-2015/22

6- Procurment of Transit Service AAU-NCB G-0013-2015/22

7- Procurment of Sport Clothes & Items AAU-NCB G-0006-2015/22

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 6 ኪሎ ዋናው ግቢ

የግዥ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ስልክ ቁጥር 011-122-00 01/011-124-32-72

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**ኦሮሚያ ክልል**

በከሳሽ ሙሉጎጃም ይሄይስ እና በተከሳሽ እነ አዲስ ዘመን የቤት ኅብረት ሥራ ማህበር እና 3 ሰዎች መካከል ስላለው የፍታብሔር ክርክር አስመልክቶ ስሙ ተስፋማሪያም ወ/ትንሳኤ የተባለው 3ኛ ተከሳሽ ቀርቦ እንዲከራከር ወይም እንዲቀርብ ሆኖ፣ የማይቀርብ ከሆነ መብቱ ታልፎ ክርክሩ እሱ በሌለበት የሚቀጥል መሆኑን እንዲያውቁ የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ችሎት**

## ማስታወቂያ

የአክሲዮን ባለቤት የሆኑት አቶ ልንገረው ለገሰ ኃ/ማርያም የሐበሻ ሲሚንቶ አ.ማ ሰርቲፊኬት ቁጥር 00852 ብዛት 10 ብር 10,000.00 (አስር ሺ ብር) ዋጋ ያለው የአክሲዮን መለያ ቁጥር ከ 016503 እስከ 016512 የሆነ ጠፋብኝ ብለው በ27/01/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡

ስለሆነም ሰርተፊኬቱን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ መንገድ ይገባኛል የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15 ቀን በሐበሻ ሲሚንቶ አ.ማ መስሪያ ቤት አሎምፒያ ጌቱ ኮሜርሻል ህንፃ 8ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 804 በሚገኘ ቢሮአችን የያዘበትን ምክንያት እንዲገልጹ እየጠየቅን፤ ይህ ባይሆን ግን ተለዋጭ ሰርተፊኬት የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**ሐበሻ ሲሚንቶ አክሲዮን ማህበር**

## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

የፍ/ባለመብት እነ ወ/ሮ አብርኸት ተ/ኃይማኖት እና በፍ/ባለዕዳ ወ/ሮ ያምሮት ሙሉጌታ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 170146 በ19/8/2008 ዓ.ም መ/ቁ 99752 በ28/9/2007 ቀን 2010 ዓ.ም በ 30/3/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 08/09 የቤ.ቁ 339 በሆነው ቤት ቤቱ በፕሮፕሮሽን 334 ካ/ሜ ቤቱ ሰነድ አልባ የሆነው የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 170,262.60(አንድ መቶ ሰባ ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ብር ከስልሳ ሳንቲም) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ታህሳስ 4 ቀን 2015 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል የተጫራቾች ምዝገባ በ4:30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያዉኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3:30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ cPO ማስያዝ ይኖርበታል:: ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም: በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬት የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን::

**በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**

ይህ ፅሑፍ ከዥንዋ የተላከ ማስታወቂያ ነው

- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትን አቋም አይገልጽም

# በምእራባውያን የሚወሰዱ የተናጠል ማእቀቦች ከታሰበላቸው አላማ በተጻራሪ አሉታዊ ጫናቸው እ ያየለ መምጣቱ ተነገረ

**አዲስ አበባ፡-** በአንዳንድ ምእራባውያን ሀገራት በኩል የሚወሰዱ የተናጠል ማእቀቦች እና እርምጃዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተበራከተ መምጣቱን ተከትሎ፤ ምሁራን በሰብአዊ መብትና መሰል ምክንያቶች ሰበብ የሚጣሉ የተናጠል ማእቀቦች ከታሰበላቸው አላማ በተጻራሪ አሉታው ጫናቸው አያየለ መምጣቱን ተናገሩ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሰብአዊ መብት ምሁር የሆኑት ዶ/ር ወንድማገኝ ታደሰ የመንግስታቱ ድርጅት መቋቋምን ተከትሎ በሀገራት መካከል በጋራ ስምምነት በተመሰረተ አግባብ የአለም አቀፍ ህጎችን ማውጣትና ማስፈጸም ትልቅ ቦታ እንዳገኘ በመናገር ነገር ግን አሁን ሁኔታዎች እየተቀየሩ እንደመጡና አንዳንድ ሀገራት ወደ ተናጠል ማእቀብ የመመለስ አዝማሚያ እያሻቀበ እንደመጣ ያስረዳሉ።

የአለም አቀፍ ህግ የማስፈጸም አቅም ውስንነት ሀገራት በግላቸው የሚወስዱትን እርምጃ ሊያበራክት እንደሚችል ገልጸው ፤ ነገር ግን የተናጠል እርምጃ ሲወሰድ ለምን አላማ ነው የሚለው ጥያቄ ያጭራል ይላሉ።

አሁን እየጨመረ የመጣው የሰብአዊ መብቶች ማእቀብ ሲሆን ይህም ሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር ፤ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለማስቆም ፤ ሰላም ለማስፈንና ጦርነቶችን ለማስቆም አየተባለ የሚጣሉ ማእቀቦች ናቸው ይላሉ።

ነገር ግን የሰብአዊ መብቶችን አስመልክቶ የሚጣሉ ማእቀቦች ህጋዊነታቸው አጠራጣሪ ነው ያሉት የሰብአዊ መብት ምሁሩ መሰል ማእቀቦች አሉታዊ ጉዳታቸው አያመዘነ መጥቷል ባይ ናችው።

"በአለም አቀፍ ደረጃ የሰብአዊ መብቶችን እንዲቆጣጠሩና አስተያየት እንዲሰጡ የተቋቋሙ አለም አቀፍ ተቋማት አሉ። የነሱን ተቋማት ግምገማ ስንመለከት የተናጠል የኢኮኖሚ ማእቀቦች መጥፎ ናቸው" በማለት "ሰብአዊ መብት እናስከብራለን ብለው የመጣስ እድል አላቸው" ዶ/ር ወንድማገኝ እንደተናገሩት፡፡

የሰብአዊ መብት ምሁሩ ከዚህ በተጨማሪም መሰል የኢኮኖሚ ማእቀቦች በብዛት ውጤታማ ሲሆኑ አይታይም ባይ ናቸው።

"እዚህ ላይ ሁለት ነገሮች አሉ፤ አንደኛ ማእቀቦቹ ውጤታማ ናቸው ወይ ስንል አይደሉም። ለዚህም የንጽጽር ማስረጃዎች አሉ፣ የታሪክ ማስረጃዎች አሉ፣ የጽንሰሃሳብ ማብራሪያ አለ ፤ ማእቀቦቹ ውጤታማ




አይደሉም" ይላሉ።

"ሰላም አሰፍናለሁ ተብሎ የተደረገ ማእቀብ ብዙ ጊዜ ሰላም ሲያደፈርስ ነው የሚታየው። ሰብአዊ መብት አከብራለሁ ተብሎ የተደረገ ማእቀብ ሲያስከብር ሳይሆን እንዲያውም በርካታ ጥሰቶች እንዲከናወኑ ሲያደርግ ነው የምናየው" ዶ/ር ወንድማገኝ ያስረዳሉ።

ውጤታማ ያልሆነ ማእቀብ ሌሎች መብቶች ሲጥስ ግን እናያለን ያሉት የሰብአዊ መብት ምሁሩ፣ ኢትዮጵያን እንደ አንድ ምሳሌ ያስቀምጣሉ። የኢትዮጵያን ከአጎአ (African Growth and Opportunity Act (AGOA)) የማስወጣት ውሳኔ አንስተው፣ መሰል ውሳኔዎች የፈለጉትን ውጤት አምጥተዋል ወይ? ሲሉ ይጠይቃሉ።

ዶ/ር ወንድማገኝ በተቃራኒው መሰል ውሳኔዎች አሉታዊ ጫናቸዉ ያመዝናል ባይ ናቸው።

አሜሪካ ራሷን አግልላ ቢሆን ኖሮ፣ ህጋዊ ነው ተብሎ ለሚታሰበው የኢትዮጵያ መንግስት ደግፉ ቢሆን ኖሮ (መሰል ቅጣቶችንና ማስፈራሪያዎችን ከመጣል በተቃራኒ) የተሻለ ውጤት ሊመጣ ይችል ይሆን ነበር ባይ ናቸው።

"ግን በተቃራኒው ማእቀቡ — ለምሳሌ ኢትዮጵያ ከአጎአ መውጣቷ FDI እንዲቀዛቀዝ፣ የኢንደስትሪ ፓርኮች ምርታቸዉ እንዲቀንስ፣ ሰራተኞች እንዲሰናበቱ እንዲሁም ለሌሎች ምክንያት ይሆናል" ያሉት የሰብአዊ መብት ምሁሩ በማእቀቦች ምክንያት የሚደርስ የኢኮኖሚ ጫና ሰብአዊ መብቶችን ይጎዳል።

"በዚህ በኩል የታሰበለትን አላማ አያሳካም፣ ግን በተቃራኒው ደግሞ መብቶችን እየጣሰ ነው" ብለዋል።

የአለም አቀፍ ግንኙነት እና የፖለቲካ ተንታኙ አቶ እዮብ በላቸው በበኩላቸው ባለፉት ጥቂት አመታት የተናጠል እርምጃዎች መበራከት እንዳሳየ ጠቅሰው በአፍሪካ ላይ በዋነኝነት ቻይና እና ሩስያ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲያቸዉን ለማስፈጸም የሚሄዱበት መንገድ በአብዛኛው አፍሪካ ሀገራት ተቀባይነት እያገኘ በተቃራኒዉ ምዕራባውያን የሚሄዱበት ጠንከር ያለና ጫና ያለው የውጪ ግንኙነታቸውን የማስፈጸሚያ መንገድ በአፍሪካውያን ዘንድ የመወገዝ አይነት ሁኔታ ሰላለ ያንን ለመቀልበስ እየሄዱበት ባለው መንገድ ዱላውን እንዲያበረቱ አድርገዋቸዋል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል።

የምራባውያን የተናጠል ማዕቀብ እየጨመረ የመጣበትን ምክንያት ሲያብራሩ እንደ ምክንያትነት ከጠቀሷቸው መካከል ሀገራቱ የጋራ የሆነ መከባበር እና አቅም ላይ የተመሰረተ የውጭ ግንኙነት መከተል እንዳለባቸው ይመክራሉ።

ለዚህም ቻይና እያበረከተች ያለውን መንገድ እንደ ምሳሌ ያስቀምጣሉ። ይህም በዋናነት የሀገርን ሉአላዊነት፣ የግዛት አንድነትን ያስጠበቀና በጋራ ጥቅም እና መግባባት ላይ የተመሰረተ የሀገራት ግንኙነትን መገንባት እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ።

"እነሱ መንግስት መለወጥ በፈለጉ ቁጥር፣ ኢኮኖሚውን በራሳቸው ሰዎች ማስተዳደር በፈለጉ ቁጥር ወደ ስልጣን ሊያመጡዋቸው በፈለጉት አካላት እና ስልጣን ላይ ባለው አካል መካከል በሚፈጠር ግጭት መካከል ህዝቦች እያለቁ ነው ኢኮኖሚው እየደቀቀ ነው። ኢትዮጵያን በዚህ እንደምሳሌነት መጥቀስ እንችላለን" በማለት አቶ እዮብ ያስረዳሉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፐብሊክ ፖሊሲ ምሁር የሆኑት ዶ/ር ቆስጠንጢኖስ በርሄ በበኩላችው በሰብአዊ መብትና ዲሞክራሲ ስም የሚጣሉ የተናጠል ማእቀቦች የሚያመጡት ጉዳት በአብዛኛው በሀገራት እና ዜጎች ላይ የሚስተዋል ሲሆን ይህም በሀገራት እድገት ላይ አሉታዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫናዎችን ያስከትላል ይላሉ።

"በአለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ, በርካታ መሳሪያዎች አሉ። በእርግጥ ዲፕሎማሲ ዋናው መሳሪያ ሲሆን ይህም ሀገራት በተባበሩት መንግስታት ወይም ባሏቸው ክልላዊ ድርጅቶች መነጋገር የሚችሉበት ነው። ስለዚህም ማዕቀቦች በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ እና በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ስምምነት ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው" ይላሉ።

ለተጠቀሱት ችግሮችም የፐብሊክ ፖሊሲ ምሁሩ እንደመፍትሄ ሀገራት በመግባባት ላይ ትልቅ ትኩረት በማድረግ ብሎም በጋራ ችግሮችን የመፍታት ልምድ በማጎልበትና የተናጠል እርምጃዎችን ለማስቀረት እንዲሰሩ ይመክራሉ።

## ከተናጠል ማእቀቦች መበራከት በስተጀርባ

የሰብአዊ መብትን ለማስከበር የሚደረጉ እርምጃዎች በአብዛኛው ጥሩ ቢሆኑም በዋናነት ድብቅ የራስ አላማን ለማስፈፀም የሚደረጉ በመሆኑ አሳሳቢ ናቸው ይላሉ ዶ/ር ወንድማገኝ።

"ለተቀደሰው የሰው ክብር፣ ለሰላም ከሆነ ጥሩ ነው። ግን ችግሩ ምንድን ነዉ በዋናነት ለዛ ሳይሆን የራስን የጂኦ-ፖለቲካዊ ይዞታ ለማሻሻል፣ በተዘዋዋሪ የሚፈልጉትን ለማስፈጸም፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ እርዳታዬን አልሰጥም፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ የንግድ ዕድል አይሰጥም አይነት ነገር ነው።"

"ከዚህ አንፃር የጂኦ-ፖለቲካዊ አዝማሚያ ነው ያለው" ከዚህም ባለፈ ሀገራት መሰል የኢኮኖሚ ማእቀቦችን በሚጥሉበት ጊዜ የሚያሳዩት ባህሪን ከግምት ውስጥ በማስገባት ምሁሩ መሰል ማእቀቦች ሁሉንም ሀገራት በእኩልነት የሚያዩበት ሁኔታም እንዳለ ያስረዳሉ።

"የጂኦ-ፖለቲካዊ ጉዳይ፣ ሀይልን የማሳያ ጉዳይ፣ የራስን ፍላጎት የማስፈጸሚያ መንገድ ነው። ባይሆንማ ሰብአዊ መብት አስከብራለሁ ብሎ የተጣለ ማእቀብ ውጤት እንደሌለዉ ሲያዩ ይተው ነበር" ዶ/ር ወንድማገኝ ያክላሉ።

በተጨማሪም መሰል ውሳኔዎች በተለይ በአሜሪካ እና ምዕራባውያን በኩል በተናጠልም ሆነ በቡድን ያላቸውን ፍላጎቶች ለማስፈጸምያነት የሚመስሉ እንደሆነ ያስረዳሉ።

"ሰብአዊ መብቶች የሚጠቀሱ ከሆነ ፍፁም በሆነ መልኩ ስለሰብአዊ መብቶች መሆን አለበት ግን አሁን እንደሚታየው እንደዛ አይደለም" ይላሉ።

"እንዲያውም ስለሰብአዊ መብቶች ብዙም የሚጨነቁ አይመስልም። ልዩ የሆነ መጮህ፣ ልዩ የሆነ ማውገዝ እና ልዩ የሆነ ማዕቀብ አለ። ይህም የሚያሳየው እነሱን የሚጋፉቸው ኢትዮጵያን እና ሌሎች ታዳጊ ሃገሮችን አስመልክቶ የጂኦ-ፖለቲካዊ እንጂ የታዳጊ ህግር ህዝቦች መብታቸው ስለተጣሰ ነው የሚል እምነት የለኝም" ዶ/ር ወንድማገኝ ያክላሉ።

በመጨረሻም ምሁሩ የሰብአዊ መብቶች ከማስጠበቅ፣ ሰላምን በማስፈን እንዲሁም መሰል አወንታዊ ጉዳዮች ስም የሚደረጉ የተናጠል ማእቀቦችና እና እርምጃዎች በተጠናና አሉታዊ ሚና እንዳይኖራቸው በጥንቃቂ መታየት አለባቸው ይላሉ።

የሰብአዊ መብቶች ሲጣሱ ያሳዝናል ነገር ግን የተቀደሰውን የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ለራስ የፖለቲካ፣ ለራስ ሀገራዊ ጥቅም ማስፈጸምያ የማድረግ ነገር ይታያል" ይላሉ።

የሰብአዊ መብት ምሁሩ ለተጠቀሱት ችግሮች እንደ መፍትሄ ሀገራት በስምምነት ላይ የተመሠረተ የጋራ ውሳኔዎችን እና ድርጊቶችን በማጎልበት እንዲሁም የተናጠል እርምጃዎችን መቀነስን ያስቀምጣሉ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የአለም አቀፍ ግንኙነት እና የፖለቲካ ተንታኙ አቶ እዮብ የተናጠል ማእቀቦች እና እርምጃዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ በአፍሪካ ሀገራት ላይ ይበልጥ እየጠነከሩ ብሎም በታዳጊ ሃገራት ላይ እያመጡ ያሉትን አሉታዊ ጫና መበራከት ከግምት ውስጥ በማስገባት ምዕራባውያን ሀገራት ድርጊታቸውን ቆም ብለው እንዲያዩ ይመክራሉ።

# ስፖርት

## ከማይዘነጉ የዓለም ዋንጫ ምርጥ ክስተቶች መካከል

**ብርሃን ፈይሳ**

በእግር ኳስ ወዳጆች ዘንድ የሚናፈቀው የዓለም ዋንጫ በኳታር ሊካሄድ 14 ቀናት ብቻ ይቀሩታል። በትልቋ አህጉር እስያ ለሁለተኛ ጊዜ በአረብ ምድር ደግሞ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄደውን ይህንን የዓለም ዋንጫም ትንሿ ከበርቴ አገር ኳታር ልታስተናግደው ዝግጅትን ጨርሳለች። በመካከለኛው ምስራቅ ግዙፍ ኢኮኖሚ ከሚያንቀሳቅሱ ሃገራት መካከል አንዷ የሆነችው ኳታር ዝግጅቷን አጠናቃ እንግዶቿን በመጠባበቅ ላይ ትገኛለች። የስፖርት ቤተሰቡም የዓለም ምርጥ ብሄራዊ ቡድኖች ለዋንጫ የሚያደርጉትን ፍልሚያ ለመመልከት በጉጉት እየተጠባበቀ ነው።

ይህንን ተከትሎም በዓለም ዋንጫ ታሪክ የማይረሱ ክስተቶችን በዛሬው ስፖርት ማህደር አምዳችን የምንዳስሰው ይሆናል። የዓለም ዋንጫ ሲነሳ ብራዚል ቀዳሚዋ የእግር ኳስ ሀገር ስለመሆኗ፤ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ሲታወስም የምንጊዜም ኮከቡ ፔሌ ቀድሞ መጠራቱ አያጠራጥርም። በእግር ኳስ ስፖርት የምትታወቀው የደቡብ አሜሪካዋ ሀገር በታላቁ የውድድር መድረክ አምስት ዋንጫዎችን በማንሳት በድል የተንቆጠቆጠ ታሪክ ያላት ብቸኛዋ ሀገር ናት። ዓለም ዋንጫ እና ብራዚል የተገናኙት ደግሞ ስዊድን አዘጋጅ የሆነችበት እአአ የ1958ቱ ውድድር ነበር። ታዲያ ይህ ወቅት በልዩነት የሚታወሰው ብራዚል የመጀመሪያውን የዓለም ዋንጫውን በማንሳቷ ብቻም ሳይሆን ታላቁ የእግር ኳስ ሊቅ ከዓለም የተዋወቀበት በመሆኑም ጭምር ነው።

እአአ 1957 የብራዚል ብሄራዊ ቡድን ከአርጀንቲና ጋር ለነበረበት ዓለም አቀፍ ጨዋታ አንድን ታዳጊ አካተተ። ብራዚል በሜዳዋ (በማራካኛ ስታዲየም) ባካሄደችው በዚህ ጨዋታም 2 ለ 1 በሆነ ውጤት መርታት ችላ ነበር። ያኔ ታዲያ የደጋፊዎች ትኩረት በድሉ ላይ ብቻ ሳይሆን በጨዋታው አንድ ግብ ባስቆጠረው የ16 ዓመት ታዳጊ ላይ ነበር። ይህ ታዳጊ በብራዚል ብሄራዊ ቡድን በትንሽ እድሜው ግብ ያስቆጠረ ተጫዋች ሆኖም ዛሬም ድረስ ይታወሳል። ይህንን ተከትሎ ለተነሳው ‹‹ይህ ተጫዋች ማነው?›› የሚለው የበርካቶች ጥያቄ ምላሹ ኤዲሰን አራንቴስ ዶ ናሲሚንቶ ወይም ፔሌ የሚል ነበር። ይህ አስገራሚ ተጫዋችም ተስፋው ቀድሞ የሚተነበይ የእግር ኳስ ክስተት ነበረና በቀጣዩ ዓመት ስዊድን አዘጋጅ በሆነችበት የዓለም ዋንጫ በሚካፈለው ብሄራዊ ቡድን አባል ለመሆን ቻለ።

በዓለም ዋንጫው ብራዚል በቡድን አራት ከሩሲያ፣ እንግሊዝ እና አውስትራሊያ ጋር ነበር የተደለደለችው። ከቡድኑ አባላት መካከል አንዱ የሆነው የ17 ዓመቱ ፔሌ ግን በጉልበት ጉዳት ምክንያት ሁለት ጨዋታዎች ላይ ሊሰለፍ አልቻለም። ከጉዳቱ አገግሞ በተካፈለበትና ከሩሲያ ጋር በነበረው የምድቡ ሶስተኛ ጨዋታ ላይም ግብ ከሆኑት ሁለት ኳሶች መካከል አንዱን በማቀበል ብቃቱን ሊያሳይ ቻለ። ከምድቧ ቀዳሚ በመሆን



**የዓለም የምንጊዜም ምርጡ ተጫዋች ፔሌ፤**

ወደ ሩብ ፍጻሜው ያለፈችው ብራዚል ከዌልስ ጋር በነበራት ጨዋታ ደግሞ ወጣቱ ፔሌ ያስቆጠራት ብቸኛ ጎል ቡድኑን ወደ ግማሽ ፍጻሜው ሊያሸጋግር ችሏል።

የግማሽ ፍጻሜው ጨዋታ በብራዚልና ፈረንሳይ ብሄራዊ ቡድኖች መካከል ሲካሄድም፤ ባልተጠበቀ ሁኔታ የብራዚል ብሄራዊ ቡድን እና ፔሌ አስደናቂ ብቃታቸውን አሳዩ። ቡድኑ አውሮፓዊቷን ተጋጣሚውን ከረታበት 5 ግቦች መካከል ተዓምረኛው ተጫዋች ፔሌ ሶስቱን በማስቆጠር በዓለም ዋንጫ ታሪክ ሶስታ(ሐትሪክ) የሰራ ትንሹ ተጫዋች በሚልም ተመዘገበ። ይህም የስፖርት ቤተሰቡን ትኩረት ሙሉ ለሙሉ ሲወስድ የስፖርት መገናኛ ብዙሃን አርዕስቶችም በወጣቱ ተጫዋች ላይ የተቃኙ ሆኑ።

በፍጻሜው ጨዋታም ብራዚል ከአዘጋጇ ስዊድን ጋር ተገናኘች። አስደናቂ በነበረው በዚህ ጨዋታ ላይም አረንጓዴና ቢጫ ለባሾቹ በተመሳሳይ ለግማሽ ደርዘን አንድ የቀረው ግብ አስቆጠሩ። ብራዚልም 5ለ2 በሆነ ሰፊ የግብ ብልጫ ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም ዋንጫን የግሏ በማድረግ ከእግር ኳስ ባለታሪኮች ተርታ ለመሰለፍ በቃች። ከተቆጠሩት ግቦች መካከል ሁለቱን ኳሶች በ55ኛው እና 90ኛው ደቂቃ ከመረብ ያዋሃደው ደግሞ በታላቁ የውድድር መድረክ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው ወጣቱ ኮከብ ፔሌ ነበር። በዚህም ተጫዋቹ በአጠቃላይ ያስመዘገባቸው ግቦች ቁጥር ስድስት በመድረሱ፤ ምርጥ ወጣት ተጫዋች በሚል ሊመረጥ ቻለ።

ከጨዋታው በኋላ የስዊድኑ ተጫዋች ሲግቫርድ ፓርሊንግ ፔሌን አስመልክቶ በሰጠው አስተያየት አድናቆቱን ሳይሸሽግ ‹‹እውነት ለመናገር ፔሌ አምስተኛውን ግብ ሲያስቆጥር፤ ላጨበጭብለት ፈልጌ ነበር›› ብላል። ባርኔ ሮናይ የተሰኘው ጸሐፊ ደግሞ ‹‹ምንም ሳይሆን ችሎታው ነበር የሚመራው፤ ይህ የመጀመሪያው ጥቁር የዓለም ምርጥ ተጫዋች ነው›› በማለት ገልጾታል ፔሌን።




## ባለህልሞቹ ታታሪ እህትማማቾች

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ልጆች እንዴት ናችሁ፤ ትምህርቱ እንዴት ነው? በደንብ ተጀምሯል አይደል? እንደውም የሴሚስተሩ ፈተና እየተቃረበ እንደሆነ ይሰማኛል። ስለዚህም በደንብ እያጠናችሁ እንደሆነ አስባለሁ። ደግሞ እናንተ ጎበዞች ስለሆናችሁ ለፈተና ብቻ በሚል አትዘጋጁም። ሁልጊዜ አንባቢ ናችሁ። ይህንን ግን አጠናክራችሁ መቀጠል አለባችሁ። ምክንያቱም አንባቢ ካልሆናችሁ ውጤታማ መሆን አትችሉም። በዚያ ላይ ህልማችሁ ላይ በምንም መልኩ አትደርሱም።

ልጆች ምን መሆን ትፈልጋላችሁ? መምህር፣ ዶክተር፣ ፖሊስ፣ ኢንጂነር፤ ተመራማሪ ወዘተ እያላችሁ ዘረዘራችሁ አይደል? ግን ይህንን ማወቅ ብቻ ህልማችሁ ላይ አያደርሳችሁም። ከዚያ አለፍ ያለ ተግባር መከወን አለባችሁ። አሁን ባላችሁበት ደረጃ ማድረግ የምትችሉት ደግሞ አንድና አንድ ነው። ፍላጎታችሁን መሰረት አድርጋችሁ መንቀሳቀስና በትምህርታችሁ ጎበዝ መሆን። ይህንን እውን ያደረጉ ሁለት እህትማማቾችን ለዛሬ ይዤላችሁ ቀርቤያለሁ። ስለዚህም ከእነርሱ ተሞክሮ ወስዳችሁ ህልመኛ ብቻ ሳይሆን ታታሪም ልጅ መሆን አለባችሁ።

መጀመሪያ ያነጋገርኳት ልጅ አኒታ ሙሴ ትባላለች። እድሜዋ ስምንት ቢሆንም በጣም ተግባቢና ንቁ ልጅ ናት። ሰው በጣም ትወዳለች፤ ያልገባትን መጠየቅ፣ የማታውቀውን ጠይቆ መረዳትም መለያ ባህሪዋ ነው። በትምህርት ቤቷ በጣም ጎበዝ ተማሪ ስትሆን በየክፍል ደረጃው ላይ የተማሪዎች ተወካይ በመሆን ተማሪዎችን ታገለግላለች። አሁንም ይህንኑ ተግባሯን እንደቀጠለች ነው።

ልጆችዬ አኒታ የሦስተኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን፤ ፊሊፐርስ ኢንተርናሽናል ትምህርት ቤት ነው የምትማረው። በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎችን በማገዝ በኩል ያላሰለሰ ጥረት የምታደርግ ልጅ ነች። በዚህም ተማሪዎች በጣም ይወዷታል። እርሷም ብትሆን ፍቅሯንም ሆነ እውቀቷን እንዲሁም ያላትን ነገር ሳትሰስት ትሰጣቸዋለች።

አኒታ መሆን የምትፈልገው ጠቅላይ ሚኒስትር ነው።



**ተማሪ አኒታ ሙሴ**



**ተማሪ ናኦሚ ሙሴ**

ምክንያቷ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ በተፈጥሮም ሆነ በእውቀት የታደለ የለምና ዓለም አገራት ይህንን እንዲያውቁ ማድረግ ትፈልጋለችና ነው። በተጨማሪም በሀገራችን የሴት ጠቅላይ ሚኒስትር ባለመኖሩና አገር በመምራት ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ሀላፊነት ለመወጣት ስለምትፈልግ ነው።

‹‹ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን በደንብ አገርን ማወቅ ያስፈልጋል፤ አገር ወዳድ መሆንም እንዲሁ። ከዚህ ትይዩ በትምህርት ጎበዝ መሆን ግድ ነው›› ትላለች። ስለዚህም ለዚህ የሚያበቃትን ሥራ ከወዲሁ እያከናወነች ነው። አንደኛው ትምህርቷን በአግባቡ መከታተልና በፕሮግራም ማጥናት ነው። ለዚህ ደግሞ አክስታችን የሚሏት ሩት የምትባል አስጠኚ አለቻቸውና በብዙ መልኩ ታግዛቸዋለች። ጨዋታቸውን ጭምር ከትምህርት ጋር በማያያዝ ስለሚጫወቱ ውጤታማ ለመሆን እንዳገዛትም ትናገራለች። ሌላኛው አኒታ የምታደርገው ነገር አመራርን ከትምህርት ቤት ጀምራ እየተለማመደችው መሄድ ነው። እስከ አሁን በነበራት ቆይታም ትምህርት ቤቱ የሚሰጣትን ኃላፊነት ተቀብላ በውጤታማነት አከውናለች።

አኒታ ለልጆች የምትመክረው ነገር አለ። የመጀመሪያው ትምህርታችሁን ውደዱ፤ ለሕልማችሁ ሥሩ የሚል ሲሆን፤ ሌላው አገር ወዳድና አገራችሁን የምታውቁ ሁኑ የሚል ነው። አትችሉም የሚሏችሁን ሰዎች ችላችሁ በማሳየት አሳምኗቸው። በመጨረሻ ጓደኞችሁን ስትመርጡ በአለው ቁስና ብልጭልጭ ነገር ሳይሆን ባለው ሰውኛ ባህሪ ብቻ መሆን አለበት የሚል ነው።

ሁለተኛ ያነጋገርኳት ልጅ የአኒታ ታላቅ እህትን ናኦሚ ሙሴን ነው። የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ነች። እድሜዋ ደግሞ 10 ነው። እርሷም እንደ እህቷ በትምህርቷ ጎበዝ ስትሆን፤ የክፍል ተጠሪ በመሆን የሚሰጧትን ኃላፊነቶች በትጋት የምትወጣ ነች። ስዕል መሳል በጣም ትወዳለች። ይህ ፍላጎቷ ደግሞ ተፈጥሮን አድናቂ አድርጓታል። የአገሯንም ውበት በተለየ ምልከታ እንድታያት አስችሏታል።

ናኦሚ ኢንተርናሽናል ትምህርት ቤት ብትማርም የዓለም አቀፉን እውቀት ለማወቅ እንጂ አገሯን ለመተው እንዳልሆነም ታምናለች። በዚህም ሌሎች ጓደኞቿ አሜሪካና ሌሎች አገራትን ሲያደንቁ ስታይ ትበሳጫለች። ምክንያቱም በእርሷ እምነት ኢትዮጵያ ውብና የአማረ ተፈጥሮ ባለቤት ነች፤ ያልተደፈረ ማንነት ያላትና ጀግና ሕዝብ የሞላባት አገር ነች። ስለዚህም ከማንም ጋር አትወዳደርም። በዚህም ሁሌ ምኞቷ ኢትዮጵያን የሚያስጠራ ሥራ መስራት ነው። አንዱ አስጠራበታለሁ የምትለው በቴክኖሎጂው ዘርፍ የራሷ ብራንድ ያላት አገር ማስባልን ነው። ለዚህ ደግሞ የኮምፒዩተር ሳይንስ ተማሪና ተመራማሪ መሆን ሕልሟ ነው።

ልጆች ናኦሚ እንደ ቶሺባ፤ ዴልና ኤችፒ አይነት ብራንዶች በኢትዮጵያዊ ስሞች መፈልሰፍ ትፈልጋለች። በተጨማሪም በስዕል ስራዎቿ መታወቅና የምትፈልገውን መረጃ ማስተላለፍ ትፈልጋለች። ከዚህ ጎን ለጎን ልታጣው የማትፈልገው ነገርና ብሰራው የምትለው ምኞቷ ተጽዕኖ የሚፈጠርባቸውን ልጆች ማገዝ ነው። አሁንም በተለያዩ ምክንያቶች ችግር የሚያጋጥማቸውን ልጆች እያገዘች እንደሆነም አጫውታኛለች።

ልጆች ናኦሚ ህልሟን ለማሳካት አንድ ነገር ማድረግ ትፈልጋለች። በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ለፍላጎቷ ወደሚቀርበው ትምህርት በጣም ማዘንበል ትፈልጋለች። ለዚያ የሚያግዙ የተለያዩ እውቀቶችን ለመቅሰም ከኢንተርኔት ላይ ታነባለች።

ናኦሚ ለልጆች የምትመክረው ነገር የመጀመሪያው የቤተሰብ ምክር ስሙ የሚለውን ነው። ለዚህ ደግሞ ቤተሰብ የድርሻውን መወጣት እንዳለበት ታስገነዝባለች። ልጆቻቸው አገር ወዳድ፤ ስነምግባር ያላቸው፤ በትምህርታቸው ጎበዝና ለህልማቸው የሚሰሩ እንዲሆኑላቸው ሳይሰስቱ ሊመክሯቸው ይገባል ባይም ነች። ምክንያቱም እርሷና እህቷ በአባታቸውና በእናታቸው ምክር ታግዘው የሚፈልጉበት ቦታ ለመድረስ እየሮጡ ነው። በትምህርት ቤት ጭምር ተወዳጅ የመሆን መሰረታቸው እርሱ እንደሆነ ታነሳለች። እንደውም በዚህ አጋጣሚ ይህንን ላደረጉላቸው ቤተሰቦቿ ምስጋናን ታቀርባለች።

ልጆች አኒታና እህቷን እንዴት አገኛችኋቸው? ብዙ ቁምነገር አስጨበጧችሁ አይደል? በሉ ለዛሬ በዚህ ሀሳባችንን እንቋጭ። በሚቀጥለው ሳምንት በሌላ ፕሮግራም እስክንገናኝ መልካም ሰንበት ይሁንላችሁ!!